



www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

ርዕሰ አንቀጽ

# መልካም እረኛ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሣ ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ዐርባ ቀንና ዐርባሌሊት ከጾመ በኋላ የተቀደሰ ሥራውን በሚጀምር በት ጊዜ ፲፪ ደቀመዛሙርት መርጦ እንዳስከተለና እነዚህም ስለመንግሥተ ሰማያት እንዲሰብኩ ቅዱስ አርኣያውን እያመለከተ እንዳስተማራቸውና ወደ ዓለምም እንደላካቸው ታሪክ ይመሰክራል ።

ጌታችን ከዕለታት ባንዱ ከበጎቹ (ምዕመናን) መካከል ተገኝቶ ራሱን በራሱ ሲያስ ተዋውቅ በበሩ የማይገባ በሌላ ግን የሚገባ ርሱ ወንበዴም ሌባም ነው ። በበሩ የሚገባ ግን መልካም እረኛ ነው ። ካለ በኋላ መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበ ጎቹ ያኖራል በማለት ስለሰው ልጆች ፍቅር ነፍሱን አሳልፎ ለሞት እንዲሰጥ አረጋግ ጦአል ።

በተናገረው መለኮታዊ ቃሉ መሠረትም ነፍሱን ስለዓለም ቤዛ አሳልፎ ሰጥቶአል ። ተከታዮቹ የሆኑት ሐዋርያትም የአምላካቸውን አርኣያና መሪቃል በመጠበቅ ስለሰው ልጆች እኩልነትና ነጻነት ስለመንግሥተ ሰማያት ዘለዓለማዊነትና ስለክርስቶስ አምላ ክነት ስለሰዎች ፍጹም ሕያውነት በዓለም ዙሪያ መስክረዋል አስተምረዋል ። በዚያውም ችግርና መከራ ተቀብለዋል ። ከእግዚአብሔር ኃላፊነት ተቀብሎ በአርምሞ መቀመጥና ሥራንም ሳይሠሩ በስም ብቻ መከበር እንደማይገኝ የተረዱት ቅዱሳን ሐዋ ርያትና ተከታዮቹም መለኮታዊ ትእዛዙን መፈጸም ግዴታቸው መሆኑን ተረድተው የሚፈለግባቸውን ተልእኮ ፈጽመው የማያልፈውን ክብር ለመቀዳጀት በቅተዋል ።

የአባቶቻቸው የሐዋርያትንና የቅዱሳን አበውን አሠር የተከተሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያም የፓትርያርክነት ሥልጣን ከተቀበሉበት ጊዜ አንሥቶ ለክርስቶስና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሲሉ በየ ጊዜው የሚከፍሉት መሥዋዕትነት ስምን በግብር የሚገልጽ ነው ፤ በተለይም ከኅዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሚያካሂዱት የተቀደሰ ተግባር እውነተኛ የምእመናን እረኝነታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ተገኝቶአል ።

ፓትርያርክ ተክለ ሃይማኖት ኅዳር ፲፩ ቀን ፸፫ ዓ/ም በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ርእሰ ከተማ በደብረ ብርሃን በወታደሮች የተሠራውን ቤተ ክርስቲያንና የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በጎበኙበት ወቅት ብዙ ትእይንተ ሕዝብ በሰልፍ ሆኖ ፍቅር የተሞላበት የክብር አቀባበል አድርጐላቸዋል ኅዳር ፲፪ ቀን፸፫ዓ/ም ጥንታ ዊና ታሪካዊ ሥፍራ በሆነው በአንኮበር ከተማ ተገኝተው ሲጎበኙም የከተማውና የአካባ ቢው ሕዝብ በእልልታና በሆታ ሲቀበላቸው የተመለከተው ሰው የሙጀመሪያ ደስታዊ ስሜት መግለጫ ሆኖ እንደሚታየው አያጠራጥርም ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዚህም በቀር በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ በጎሐ ጽዮን ከተማ ኅዳር ፳፩ ቀን ፸፫ ዓ/ም ያደረጉት ጉብኝት እጅግ ደማቅና ፍቅር የተመላበት ነበር ። ሕዝቡም መንፈሳዊ አባቱን በማግኘቱ (በማየቱ) የተሰማው ደስታ ወሰን አልነበረውም ።

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስነታቸው ጉብኝታቸውን በመቀጠል በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ከታኅሣሥ ፲፮ እስከ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፹፫ ዓ/ም ድረስ ታሪካዊ ጉብኝት አድርገዋል ፤ የሐረርጌ ክፍለ ሀገር ሕዝብም ለቅዱስነታቸው ልባዊ ፍቅር የተመላበት አቀባበል አድርጎላቸዋል ። በዚሁ ጉብኝታቸው በድሬደዋ በሐረር ከተማና በቁልቢ ገዳም እየተዘዋወሩ አብያተ ክርስቲያናት ጥንታውያንና ታሪካውያን የሆኑትን ሥፍራዎች ቅርሳቅርሶችና ንዋያተ ቅድሳትም ተመልክተዋል ። ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ምሁራንም አነጋግረዋል ። ስለጉብኝታቸውም ከሊቃውንቱ የቀረቡትን መወድስ ቅኔዎችም በጽሞና አዳምጠዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዚሁ ጉብኝታቸው ያዘኑትን ረድተውና አጽናንተው ለየአብያተ ክርስቲያናቱም የገንዘብ እርዳታ ሰጥተው ታኅሣሥ ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በሄዱበት አኳኋን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያሪኩ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ርእሰ ከተማ በላልይበላ ከታኅሣሥ ፳፰ እስከ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፹፫ ዓ/ም ድረስ ያደረጉት ታሪክካዊ ጉብኝት ይበልጥ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከመያዙም በላይ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከፍተኛ መንፈሳዊ ተሐድሶ እንዳስገኘላት የማይታበል ሐቅ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ይህ ዝነኛና ታሪከኛ የሆነ የቅዱስ ላልይበላል ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት በጐበኙበት ወቅት በቁጥር የማይለካውን ሕዝብ የቅዱስነታቸውን መምጣት በግራማፎን በተበሰረለት ጊዜ ይሰማ የነበረውየ ዕልልታ ድምፅ ከፍተኛ ነበር ። በተለይም ቅዱስነታቸው በሕዝቡ መሐከል ተገኝተው ቃለምዕዳን በሰጡበት ወቅት የነበረው የሕዝቡ ደስታ ምን ያህል እንደሆነ ለመግለጽ ቃላት አይገኝለትም ።

ቅዱስነታቸው በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው የቅዱስ ላልይበላልን አብያተ ክርስቲያናት ዳገቱን ቁልቁለቱን በመውረድና በመውጣት አንድ በአንድ ሲጎበኙ ዕረፍት አልፈለጉም ስለሆነም ዳገት ቁልቁለቱን በመውጣትና በመውረድ የየአብያተ ክርስቲያናቱ ችግር መፍትሔ በመስጠትና ካህናቱንም በመርዳት ከአንድ የሃይማኖት መሪ የሚፈለገውን መሥዋዕትነት ከፍለዋል ። ፓትርያርኩ ይህን ሁሉ እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ በእግር ረግጦ፤ በአይን አይቶ መምጣት ብቻ ሳይሆን የገንዘብና የልዩ ልዩ ንዋያተ ቅዱሳት ስጦታንም በመለገስ በመቸውም ጊዜ ታይቶ የማይታወቅ የተቀደሰ አርአያ አሳይተዋል ።

ከዚህም ቀጥሎ ቅዱስፓትርያርኩ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ከጥር ፭ እስከ ጥር ፳፩ ቀን ፹፫ ዓ/ም በርእሰ ከትማው በአሥመራና በምጽዋ የሚያደርጉትን ጉብኝት ፈጽመው ተመልሰዋል ።

ቅዱስነታቸው ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ ም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳትን አስከትለው አሥመራ አራተኛ ዮሐንስ አእሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ ጓድ ኮሎኔል ፍቅሩ ወልደ ተንሣይ ፤ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችና የከተማው ሕዝብ እንዲሁም የገዳማትና የአድባራት አለቆች ፤ ካህናት ፤ መዘምራንና የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት በክብርና በደማቅ ሁኔታ ተቀብለዋቸዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ጉዞአቸውን ወደ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤ/ክርስቲያን በማምራት በዚያው ተሰልፎ መምጣታቸውን ይጠባበቅ የነበረውን ሕዝብ ቃለምዕዳንና አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል ከዚያም በማከታተል በወጣው መርሐ ግብር መሠረት የሚያደርጉትን የሥራ ጉብኝት ፈጽመው ጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በሄዱበት አኳኋን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከየካቲት ፫ እስከ የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በከፋና በኢሉባቦር ክፍላተ ሀገራት ከየካቲት ፲፪ እስከ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በዚሁ ተመሳሳይ በወለጋ ክፍለ ሀገር ጉብኝት አድርገዋል ።

በእነዚሁ ክፍላተ ሀገራት ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት አውራጃዎችና ወረዳዎችም ጭምር የጎበኙ ሲሆን ከክፍላተ ርእሳነ ከተማዎች ጀምሮ እስከ ወረዳዎቹ የሚገኙት ሕዝበ ክርስቲያንም የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ጉብኝት የተሰማቸውን ደስታ ከፊታቸው ይነበብ ነበር ።

ፓትርያርክ ተክለ ሃይማኖትም ያለ አንዳች ድካም የሚፈለግባቸውን አባታዊ ግዴታ እየተዘዋወሩ ምእመናን ልጆቻቸውን አንድ በአንድ ጎብኝተው ምዕዳንና ቡራኬም ሰጥተው በምግባርና በሃይማኖት እንዲጸኑም ትምህርታዊ ምክር አሰምተው ወደ አዲስ አበባ መንበረ ካናቸው ተመልሰዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ባጭር ታጥቀው ዕርፈ መስቀላቸውን ጨብጠው ምእመናን መንጎታቸውን ከነጣቂ ተኩላዎች ማለት ከጅሆባ፤ከባሐኡ ላህና፤ከመሳሰሉት መሠርያን ድርጅቶች ለመከላከል የተጣለባቸው ከባድ ኃላፊነት በሥራ ተርጉመው ለማሳየት እንደአባታቸው እንደአቡነ ተክለ ሃይማኖት በመላ የኢትዮጵያ ሀገረ ስብከቶች እየተዘዋወሩ በረከታቸውና ረድኤታቸውንም ለበጎች ምዕመናኖቻቸው ለማስተላለፍ እንደተዘጋጁ የታመነ ነው ።

ስለዚህ ሊቃነ ጳጳሳት ፥ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት መምህራንና ሰባክያንም የመልካም መሪያቸውን የተቀደሰ ሥራና ዋና ምግባር ተከትለው የሚፈለግባቸውን መንፈሳዊ ተልእኮ ለመፈጸም እንደተነሣሱ እሙን ሆኖ ተገኝቶአል ።

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊም በተሰለፈበት ዓላማ ስለ እውነት በእውነት ሠርቶ ከተገኘ ምንደኛ ከሚባል የነቀፌታ ስም ወጥቶ መልካም እረኛ ፤ ሰነፍ ከመባል አልፎ ገብር ኄር ማለት መልካም አገልጋይ ተብሎ ለመጠራት ይበቃል፤ ይህንኑ ስም ለመቀዳጀት ከፍተኛ ድካምና ውጣ ውረድ ያለበት ቢሆንም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ተወካይ ምድራዊ ሰውነት ለሰማያዊ ክብር ሲል ሳይሰቀቅ ግዴታውን መወጣት አለበት። ይኸውም ምዕመናን መንጎቹን በለመለመ ሣርና በጠራ ውኃ እያሰማራ ከነጣቂ ተኩላ ተግቶ ቢጠብቃቸው መልካም ዕረኛ ስለበጎቹ ቤዛ ሕይወቱን ይሰጣል ወይም ይለውጣል ተብሎ እንደተነገረው ሁሉ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳትም ፤ እንዲሁም ሰባክያነ ወንጌልና መምህራን ቡቲጣለባቸው አምላካዊ አደራ መሠረት ምእመናን መንጎቻቸውን ፤ ከጅሆባ ፤ ከባሃኡላህና ፤ ከክርስቶስ ወንጌል መንገድ ላይ መሰናክል ከሚያስቀምጡት መሠሪያን ድርጅቶች እንዳይነጠቁ እየጠበቁ ጥሩ የወንጌል ቃል እየመገቡ ፤ በንስሐ እያደሱና በሥጋው ወደሙ እያጎለመሱ ለመንግሥተ እግዚአብሔር እንዲያበቁ ሌት ተቀን መድከም ይገባቸዋል ። እንደነዚህ ያሉት ሁሉ መልካም እረኛ ተብለው ተሰይመዋልና መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ (ስለምዕመናኑ ) ያኖራል ተብሎ በመለኮታዊ ቃል ተነገሮአልና ።

www.ethiopianorthodox.org

# ቃ ለ ም ዕ ዳ ን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ።

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን ፤

በዓለ ትንሣኤን ለማክበር በዝግጅት ላይ የምትገኙ በከተማም በገጠርም ያላችሁ ፣ የተወደዳችሁ ምእመናን ፤ የሰላም አምላክ መዋዕለ ጾሙን በደህና አስፈጽሞ ለብርሃነ ትንሣኤው እንኳን በደኅና አደረሳችሁ ፤

ይህ ዕለት ለብዙኃን ቤዛ ክቡር ደሙን በመስቀል ላይ ያፈሰሰውና ራሱን ለሞት አሳልፎ የሰጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞት በመደምሰስ በእርግጥ የሕያዋን ሕይወት የሙታን ትንሣኤ መሆኑን በግብር ያረጋገጠበት ዕለት ስለሆነ በዓሉ ከፍተኛ የደስታ በዓል ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞቱና ከትንሣኤው በፊት የነጻነት ወንጌልን ለዓለም በሚሰብክበት ወቅት በኢየሩሳሌም ብዙ ጸዋትወ መከራን ይቀበል ዘንድ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዳለው ለደቀ መዛሙርቱ በግልጽ ይናገር ነበር ፤ (ማቴ ፲፮ ፳፩) ። ይህን ምሥጢር በደቀመዛሙርቱ አማካይነት ለዓለም ይገለጽ የነበረውም ሞቱም ሆነ ትንሣኤው በአምላካዊ ፈቃድና ሥልጣን የሚፈጸም አምላካዊ ግብር እንጂ ግብታዊና ዓለማዊ አለመሆኑን በቅድሚያ ለማስረዳት እንደነበር ግልጽ ነው ፤ የሰው ልጆች ቤዛ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንዱ በኩል ከሞቱና ከትንሣኤው በፊት ስለሞቱና ትንሣኤው በዚህ ዓይነት ለዓለም ሲገለጽበሌላበኩል ደግሞ «እነሆ የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሷል እውነት እውነት እላችኋለሁ የስንዴ ፣ ቅንጣት በምድር ላይ ካልወደቀችና ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ፤ ከሞተች ግን ብዙ ፍሬን ታፈራለች በማለት ስለሞቱ ሕይወትነት በምሳሌ ዘር ይናገር ነበር (ዮሐ ፲፪ ፳፬)። በምሳሌው እንደተገለጸውና ሁሉም እንደሚያውቀው አንዲት ቅንጣት ዘር በአፈር ላይ ወድቃ ካልሞተች አትነሣም ፤ ወይም አትበቅልም ፤ ካልበቀለችም በእርግጥ አታፈራም ።

ምሳሌው ምንጊዜም የመሥዋዕትነት አስፈላጊነትና ፍሬያማነት በገቢር የሚያረጋግጥ ሲሆን የክርስቶስ ደም ደግሞ በሕይወትነቱና በፍሬያማነቱ ከመሥዋዕት ሁሉ የበለጠ መሥዋዕት ስለሆነ በሞተ ኃጢአትና በሞተ ኅሊና ጥላ ሥር ለነበሩና ለሚኖሩ ሁሉ በእርግጥ ትንሣኤና ሕይወት ነው ።

ይህ በመሆኑም እኛም ሆነ ሌሎች በዓለም ላይ የሚገኙ ዕልፍ ሕያዋን ምእመናን በኅብረት እግዚአብሔር እናመሰግናለን ፤ በዓለ ትንሣኤውንም በየዓመቱ በደስታ እናከብራለን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ የመሰለው ምሳሌ ዘር ሁሉንም የሚመለከት ዓቢይ ምሳሌ ነው ። የሰው ልጅ የሚኖረው ጽድቅና ኃጢአት ፤ ድቀትና ትንሣኤ ፤ ደስታና ችግር ፤ ሰላምና ሽብር ሊፈራረቅበት በሚችል ዓለም ላይ ስለሆነ ለዚህ ዓለም ሰላምና ለሰው ልጅ ደኅንነት የሚያስፈልገውን ጽድቅ ሁሉ ለመፈጸም በእርግጥ መሥዋዕትነት ያስፈልጋል ።

በዓለም ላይ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው ። በዓለም ላይ እውነተኛሰላምከሌለየሰውልጅድካምናጥረቱ ሁሉ ከንቱ ነው ። ተሠርቶ ይፈርሳል ፤ ጌታ



ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በደቀመዛሙርቱ አማካይነት ለሰው ልጆች ሁሉ ያስተላለፈው መልእክት «ሰላም ለኵልክሙ ማለት ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» የሚል ነበር (ዮሐ ፳ ፲፱—፳፯) ። «ሰላም ለሁላችሁ » ማለትም ሰላም በምድር ማለት ነው ። ይህንም የሚያመለክተው ምንጊዜም የሰላምን አስፈላጊነት ነው ።

ሰላም በእርግጥ ለሁሉም በሁሉ ቦታ ያስፈልጋል ፤ በዓለም ላይ በአንድም ቦታ እውነተኛ ሰላም ሳይኖር «ሰላም ለሁላችሁ» ወይም ሰላም በምድር «በሚለው መርህ መሠረት የዓለም ሰላም የተሟላ ሊሆን አይችልም ። እውነተኛ ሰላም ሊኖር የሚችለውም በሰዎች መካከል ዕውተኛ ፍትሕና ርትዕ ሲኖር ነው ። በራስ ወዳድነት አንዱ የሌላውን የሚመኝና እንዲሁም የሌላውን ነጻነት የሚደፍር ከሆነ እውነተኛ ሰላም በሰዎች መካከል ሊኖር አይችልም ። ይህም ከሆነ ዘንድ በዓለም ላይ እውነተኛ ሰላምና ፍቅር ፍትሕና ርትዕ ይሰፍን ዘንድ ምንጊዜም የቤተ ክርስቲያን ምኞትና ጸሎት ነው ።

«ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሃደ» ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ ትንሣኤውንም ገለጠ ።

የሰላም አምላክ ለዓለም ሰላምን ለሀገራችን ደኅንነትንና ብልጽግናን ይስጥልን ።

ኢትዮጵያን በአንድነትና በነጻነት ለዘለ

ዓለም ይባርክ አሜን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ፓትርያርኩ ጉብኝት በክፍለ ሀገራት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር በየክፍላተ ሀገሩ የሚያደርጉት ጉብኝት እንደቀጠለ ነው ይልቁንም ከታህሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም እስከ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ድረስ በርከት ያሉ ክፍላተ ሀገራትን ጎብኝተዋል።

ይኸውም በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ቅዱስ ላልይበላል የሠራቸውን አስደናቂ የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት ከታኅሣሥ ፳፰ እስከ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ድረስ ታሪካዊ ጉብኝት አድርገዋል ።
ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በላልይበላል ከተማ የሚገኙትን ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት ለመጎብኘት ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ከአዲስ አበባ በአእሮፕላን ሲነሱ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ቆሞሳትና የታላላቅ አድባራት አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የቤተ ክህነት ሹማምንት በቦሌ አእሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው ከፍተኛ አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከላይ በተጠቀሰው ቀን ከንጋቱ ፩ ሰዓት ላይ ብፁዕ ዶክቶር አቡነ ገብርኤል በሐረርጌ ሀገረ ስብከት የምሥራቅ የሰሜንና የደቡብ አውራጃዎች ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የአርሲ ሀገረ ስብከት ጳጳስ አቶ ጸጋዬ በርሄ የሕጻናት አስተዳደግ ኃላፊ የቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ቀሲስ አባ ኃይለ ማርያምን አስከትለው በላሊበላ ሹምሸኻ አእሮፕላን ጣቢያ እንደተገኙ አቶ መርስኤ ኀዘን አበበ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬ የቅ/ፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ መጋቤ ካህናት ብርሃኑ መኰንን በኢትዮጵያ ኦርቶዊክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ ም/መጋቤ ካህናት መልአከ ምሕረት መዓዛ ወልደ ኢየሱስ ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ/ሕይወት የሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ የሰበታ ወረዳ ሰባኬ ወንጌል መምህር ከበደ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከትና ማስታወቂያ መምሪያና የሐዋርያዊ ድርጅት ጋዜጠኞች እንዲሁም ብፁዕ አቡነ ሣሙኤል የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስና አሊቃ መንበሩ ወ/አገኘሁ የወሎ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የከ. ነ. ማና የገ. ማ. አብዮት ጠባቂዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎች በከፍተኛ ድምቀት ተቀብለዋቸዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ከአእሮፕላን እንደ ወረዱ በክብር ታጅበው በላልይበላል ከተማ ክልል የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕጻናት ማሳደጊያ ድርጅትን ጎብኝተዋል በዚህ ጊዜ በድርጅቱ የሚያድጉት ሕጻናት ተሰልፈው በክብር በመዝሙርና በይባቤ አቀባበል አድርገውላቸዋል ቅዱስነታቸውም ለሕጻናቱ አባታዊ ቡራኬ ሰጥተው ወደ ቤተ ማርያም አምርተዋል በቤተ ማርያም አደባባይም የቅዱስነታቸውን መምጣት ሲጠባበቅ የነበረው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝበ ክርስቲያን መዘምራንና ሊቃውንቱ እንዲሁም ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በሆታና በዕልልታ በጭብጨባና በልዩ ልዩ ዝማሬ ተቀበሏቸው ፤ ቅዱስነታቸውም በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እንደተገኙ መምህር ብርሃነ ሥላሴ መንበሩ የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ገዳም አስተዳዳሪና የአውራጃው ቤተ ክህነት ኃላፊ የቅዱስነታቸውን መምጣት በማስመልከት ንግግርአደረጉ ፤ መምህር ብርሃነ ሥላሴ የቅዱስነታቸው ጉብኝት የተሳካ እንዲሆን ገልጸው የሚያደርጉትም ጉብኝት ለሀገሪቱ ታላቅ በረከትና ረድኤት እንደሚያስገኝና እንደሚያስጥ አረጋግጠዋል ፤በተለይም በላስታ አውራጃ ያሉት ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናትና ካህናቶቻቸው ባሁኑ ጊዜ በችግር ላይ ስለሚገኙ የቅዱስነታቸው መጥቶ መመልከት ታላቅ መድኀን እንደሚሰጠው አብራርተዋል ።

ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ሣሙኤል የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ንግግር አደረጉና ቅዱስነታቸውም ለንግግሩ መልስ በመስጠት ጸሎተ ቡራኬ ሰጡ ። በዚህም ወቅት የተመረጡት ሊቃውንት ስለቅዱስነታቸው ክብር ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔዎች አበርክተውላቸዋል ፤ የአቀባበሉ ስነ ሥርዓት በዚህ እንዳበቃ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ወደ አብያተ ክርስቲያናቱ በማምራት የቤተ መድኃኔ ዓለምንና የቤተ ማርያምን አብያተ ክርስቲያናት ጎበኙ፤ከዚያም ወደ ቤተ ማርያምቤተ መቅደስ ገብተው ከቅዳሴው ሰዓት ጀምሮ ሠርሆተ ሕዝብ እስከሆነ ድረስ ከቆዩ በኋላ ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ ሄዱ በዚያም ጥቂት ዕረፍት እንዳደረጉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሕጻናት አስተዳደር ቅጽር ግቢ ተገኝተው የሕጻናቱን ማሳደጊያ ድርጅትን መርቀው ከፍተዋል ። ከዚያም የውስጥክፍሉን አንድ በአንድ ጎብኝተዋል ።
በምረቃውም ሥነ ሥርዓት ላይ አቶ መርስኤ ኃዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅና የድርጅቱ ሊቀ መንበር ብፁዓን ጳጳሳትና የጀርመን ክርስቲያናዊ ተራድኦ ወኪሎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል ።
በዚሁ ወቅት አቶ መርስኤ ኃዘን አበበየጠ/ቤተክ/ሥራ፤አስኪያጅና የድርድቱ ሊቀመ/ አቶ ጸጋዬ በርሄ የድርጅቱ ኃላፊና የጀርመን ክርስቲያናዊ ተራድኦ ተወካይ ዶክተር ሾሬር በየተራ ንግግር አድርገዋል በመጨረሻም ቅዱስ ፓትርያርኩ ስለሕጻናቱ አስተዳደግና የጀርመን ክርስቲያናዊ ተራድኦ ስለሚያደርገው የተራድኦ ተግባር አመስግነው እንዳበቁ በጸሎት የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

ታኅሣሥ ፳፰ ለ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም አጥቢያ ሌሊቱን ሙሉ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲካሄድ አድሮአል ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ሠራዒነት በጳጳሳቱ ተራዳኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ሲካሄድ ቆይቶ እንዳበቃ ከንጋቱ በሁለት ሰዓት ላይ ሊቃውንቱ በማሜ ጋራ አፋፍ ሆነው «ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም ዮም ተወልደ ቤዛ ኵሉ ዓለም»የሚለውን ቃኝተው እንዳሸበሸቡ ብፁዕ (ዶክተር)አቡነ ገብርኤል በሐረርጌ የሰሜን የምሥራቅና ደቡብ አውራጃዎች ጳጳስ የቅዱስነታቸውን ጉብኝት በማብራራትና በዓሉንም በማስመለከት ትምህርት ሰጥተው እንዳበቁ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወደተዘጋጀላቸው ሥፍራ ገብተው ጥቂት ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ቤተ ጎልጎታን ፤ ቤተ ደናግልን ቤተ ሚካኤልንና ቤተ ጊዮርጊስን ጎብኝተው ፫ ሰዓት ሲሆን በሄዱበት አኳኋን በአእሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል በዚሁ ወቅት አቶ መርስኤ ኃዘን አበበና የቤተ ክህነት ሹማምንት ብፁዓን ጳጳሳትና ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የከ. ነ. ማ. እና የገ. ነ. ማ. የአብዮት ጠባቂዎች በሹምሸኻ አእሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው ከፍተኛ አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።

እንዲሁም ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም አቶ መርስኤ ኃዘን አበበ የቤተ ክህነት ጠ. ሥራ አስኪያጅ አባ ገብረ እግዚአብሔር





www.ethiopianorthodox.org

ፀጋዬ የፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ መጋቤ ካህ
ናት ብርሃኑ ሙኰንንና ም/መጋቤ ካህናት
መልአከ ምሕረት መዓዛ ወል ደኢየሱስ ሊቀ
ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገብረ ሕይወት የሸዋ
ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሰባጌ ወንጌል
ከበደ ተገኑ የሰበታና አካባቢዋ ሊቀ ካህናት
የስብከትና ማስታወቂያ መምሪያና የሐዋርያ
ዊ ድርጅት ጋዜጠኞች ወደ አዲስ አበባ ሲመ
ለሱ በወልድያ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅትን
በኃላፊው በአቶ ፍሥሐ ጌታነህ አማካይነት
እየተዘዋወሩ አንድ በአንድ ጎብኝተዋል ።

በዚሁ ወቅት አቶ መርስዔ ኃዘን አበበ
የቤተ ክህነት ጠ/ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪ
ያጅ ሕጻናቱ ማድረግ ስለሚገባቸውና ድር
ጅቱ ስለሕጻናቱ ማሟላት ያለበትን ግዴታ
እያነጻጸሩ ማብራሪያ ሰጥተዋል አቶ መርስኤ
ኃዘን አበበ ሕጻናቱ በቤተ ክርስቲያኑ ክልል
ሲያድጉ ለሀገርና ለወገን እንዲሁም ለቤተ
ክርስቲያን የሚጠቅም ትምህርት ቀስመው
ማደግ እንደሚገባቸው አስገንዝበው ድር
ጅቱም በግብረ ገብነታቸው በክርስቲያናዊ
አቋማቸውና በሀገር ወዳድነታቸው የታ
ወቁ ሰዎች እንዲጠብቁአቸው እንዲያአ
ስተምሩአቸውና ፡ እንዲንከባከቧቸው የማ
ድረግ ኃላፊነት የድርጅቱ ፤ መሆኑን አስ
ገንዝበው በጥብቅ አስጠንቅቀዋል ከዚህ
ቀደም ብሎ ግን ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ
ገብረ ሕይወት ስለክርስትና ትምህርት በም
ሳሌ እያነጻጸሩ ሕጻናቱን አስተምረዋቸዋል
በመጨረሻም የመንገደኞች አዳር በደሴ
ከተማ ሆኖ ጥር ፳ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም በሰላም
አዲስ አበባ ገብተዋል ።

## ጅ ማ ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ከየካቲት
፫ እስከ የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ድረስ
በከፋና በኢሉባቦር ክፍላተ ሀገራት እየተ
ዘዋወሩ ጎብኝተው ወደመንበረ ካናቸው



ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከላይ በተጠ
ቀሰው ቀን በ፩ ሰዓት ተኩል ብፁዕ አቡነ
መርሐ ክርስቶስ የኤርትራ ሀገረ ስብከት
ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት
ጳጳስ ብፁዕ (ዶክተር) አቡነ ጢሞቴዎስ
የከፋ የማጅና የጊሚራ አውራዎች ጳጳስና
የልማት ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ ሊቀ ካህናት
ዘውዴ ታችበሌ የሰበካ ጉባኤ ም/ኃላፊና
የአዲስ አበባ መካከለኛ አብያተ ክርስቲ
ያናት አደራጅ ሊቀ መንበር የስብከትና
ማስታወቂያ መምሪያና የሐዋርያዊ ድርጅት
ጋዜጠኞችን አስከትለው ከአዲስ አበባ ፪፻፷
ኪ/ ሜትር ያህል እንደተጓዙ በጅማ አውራጃ
በደነባ ወረዳ በሶኮሮ ከተማ ነዋሪ የሆነ
ሕዝበ ክርስቲያን የቅዱስነታቸውን መም
ጣት ሰምቶ በክብር ተሰልፎ ከፍተኛ አቀባ
በል አድርጎላቸዋል ቅዱስነታቸውም በዚህ
ከተማ የሚገኘውን የገነተ ጽጌ ማርያም ቤተ
ክርስቲያንን ጎብኝተው ለምእመናኑም አባ
ታዊምክርና ቡራኬ ሰጥተው ጉዞአቸውን
በመቀጠል በ፲ ሰዓት ጅማ ከተማ እንደ
ደረሱ በሸዋ በር ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የከፋ
ሀገረ ስብከት ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና
ጸሐፊ የጅማ ከተማ ከንቲባና ታላላቅ የመ
ንግሥት ባለሥልጣኖች እንዲሁም የሀገረ
ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ አሰፋ ሥዩ
ምና የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ እንደራሴ መም
ህር ገብረ ማርያም ተስፋ እና የካቶሊካዊት
ቤተ ክርስቲያን ተወካይ ቆሞስ ተክለ ሃይማ
ኖት ተስፋ በክብር ተቀብለዋቸዋል ፤ በዚሁ
አኳኋን ከከተማው እንደደረሱ ግራ ቀኙን
ተሰልፎ የቅዱስ ነታቸውን መምጣት ሲጠ
ባበቅ ለነበረው ሁሉ አባታዊ ቡራኬ እያደ
ረጉ ወደ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
ገብተዋል ከዚያ ተሰልፎ ሲጠባበቅ የቆየው
ሕዝብ በዕልልታና በሆታ በይባ ቤና በዝማሬ
ተቀበላቸው ሁለት ሕጻናትም የአበባ ዕቅፍ
እንዳበረ ከቱላቸው ወደ ቤተ መቅደስ ገብተ
ውየሕሊና ጸሎት አድርሰዋል ቀጥሎም በተዘ

ጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እንደተገኙ ብፁዕ
አቡነ ኤልሳዕ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስና የሲኖዶ
ሱ ዋና ጸሐፊ ቅዱስነታቸውን እንኳን ደህና
መጡልን ጎብኝትዎም የተቃና ና የተስተ
ካከለ ያድርግልን በማለት አጭር ንግግር
አድርገዋል ። ቀጥሎም ከሊቃውንት ስለቅ
ዱስነታቸው ክብር ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔ
ዎች ተበርክተዋል በመጨረሻም ቅዱስ
ነታቸው ቃለ ምዕዳንና አባታዊ ቡራኬ ሰጥ
ተው ወደተዘጋጀላቸው ሥፍራ ሄደዋል ፣
በዚሁ ዕለት ከምሽቱ በ፩ ሰዓት ጀምሮ ስለቅ
ዱስነታቸው ክብር በሀገረ ስብከቱ አማካ
ይነት ለመንግሥት ባለሥልጣኖች ለከተማ
ነዋሪዎችና ጥሪ ለተደረገላቸው እንግዶች
ታላቅ ግብዣ በመርሐ ጽድቅ ስብከተ ወን
ጌል አዳራሽ ተደርጎ የፕሮግራሙ ስነ ሥር
ዓት ፍጻሜ ሆኖአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
የካቲት ፬ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ልክ ሦስት
ሰዓት ሲሆን በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስ
ቲያን ተገኝተው ጉብኝት ካደረጉ በኋላ
በዚሁ አካባቢ የሚገኘው የቅዱስ ገብርኤ
ልና የኪዳነ ምሕረትን ጠበል ጎብኝተው
ሥርዓተ ጸሎቱንም አድርሰው በዚያው
ለነበሩት ምእመናን ሁሉ ቃለ ምዕዳንና
ቡራኬ ሰጥተዋል ከዚያም በጅማ ከተማ
የሚገኘውን ቤተ መዘክርና የከተማ ማዘጋጃ
ቤት ምክር ቤትን ጎብኝተዋል ቀጥሎም
የፈለገ ሰላም ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን
ጎብኝተው ቡራኬም ሰጥተው ልክ ስድስት
ሰዓት ተኩል ሲሆን በደብረ ኤፍራታ ቅድ
ስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገኘት
አስቀድሰው ወደማረፊያቸው ተመልሰዋል።

ከሰዓት በኋላ ወህኒ ቤት ኪዳነ ምሕረትን
አለን ቅዱስ ጊዮርጊስን ጎብኝተው ወደሥ
ፍራቸው እንደተመለሱ አንድ ሰዓት ሲሆን
በጅማ አጠቃላይ መርሐ ጽድቅ ስብከተ
ወንጌል አዳራሽ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅ
በር ተገኝተው ከልደት እስከ ስደት የሚያ



መለከት የጌታችን ታሪክ በወጣቶች የተ
ዘጋጀ ቲያትር ተመልክተዋል ልክ ሦስት
ሰዓት ሲሆን ወደ ተዘጋጀላቸው የክብር
ማደሪያ ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስነታቸው የካቲት ፭ ቀን
፸፫ ዓ/ም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከ
ትለው ጉብኝታቸውን ለመቀጠል ወደከፋ
አውራጃ ርእሰ ከተማ ወደቦንጋ ሄዱ ፤
በቦንጋ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያንም በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የመን
ግሥት ባለሥልጣኖች ፤ የካቶሊክ ቤተ
ክርስቲያን ተወካይ ፤ የከተማው አብያተ
ክርስቲያናት ፤ ካህናትና ወጣቶች በክብር
ተቀብለዋቸዋል ። በዚሁ ቤተ ክርስቲያን
ጸሎት አድርሰው በተዘጋጀላቸው ሥፍራ
እንደተገኙም ብፁዕ አቡነ ዶክተር ጢሞ
ቴዎስ የሦስቱ አውራጃዎች ጳጳስና የልማት
ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ እንኳን ደህና መጡ
ልን በማለት ንግግር አድርገዋል ቀጥ
ሎም ከደብሩ የሰበካ ጉባኤ መሪዎች አንዱ
የቅዱስነታቸው መምጣት የቦንጋ ሕዝበ
ክርስቲያን ከልብ ያስደሰተው መሆኑን
በንግግራቸው ላይ ገልጸዋል ።
ቅዱስነታቸውም ከዚህ አያይዘው ስለተደ
ረገላቸው ደማቅ አቀባበል ከልብ የተደሰቱ
መሆናቸውን ገልጸው ቡራኬ ከሰጡ በኋላ
የአቀባበሉ ስነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኖአል

ቅዱስ ፓትርያርኩ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ
ከቦንጋ ከተማ ሠላሳ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚ
ገኘውን በመሠራት ላይ ያለውን የአንደ
ራቻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን ጐብኝ
ተው ምእመናኑም የሰበካ ጉባኤውንም አነ
ጋግረው አባታዊ ምክርና ቡራኬም ሰጥተው
ጉዞአቸውን ወደቦንጋ አምርተዋል ምሳ
በቦንጋ ተደርጎ በ፰ ሰዓት ወደከፋ ርዕሰ
ከተማ ወደ ጅማ በሄዱበት አኳኋን ተመ
ልሰዋል ።

በጅማ ከተማም እረፍት እንኳ ሳይሹ
በቀጥታ ጉዞ ወደ ሊሙ አውራጃ ወደ አጋሮ
አመሩ አጋሮ ከተማ ከምሽቱ አንድ ሰዓት

www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስነታቸው በጅማ ሙድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንደተገኙ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የሀገረ ስብከቱ
ጳጳስ ስለቅዱስነታቸው ጉብኝት የተሰማቸውን ደስታ መግለጫ ሲሰጡ ።





ፓትርያርኩ በጅማ ከተማ አካባቢ የሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ጠበል ሲባርኩና ከተጠማቂዎቹም
አንዱን ሲያጠምቁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሲገቡ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የከተማው ነዋሪ ሕዝብ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የቀበሌ ሊቃነ መናብርት የኢትዮጵያን ባንዲራ እያውለበለቡ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ከፍ ያለና የደመቀ አቀባበል አድርጎላቸዋል በዚሁ ወቅት ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ንግግር አድርገው እንዳበቁ አባታዊ ቡራኬ ለመስጠት በነገታው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እንዲሆን ተወስኖ ወደተዘጋጀላቸው ማረፊያ ሄደዋል ።


ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከላይ እንደ ተጠቀሰው የካቲት ፮ ቀን ፸፫ ዓ/ም በማኅበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ከ፩ ሰዓት ጀምሮ እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ አባታዊ በረከት አስተላልፈዋል ከዚህም በማያያዝ የመካነ ሰማዕት ቅ/ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተውና በዚሁ ሥፍራ የተገኙትን ምእመናን ባርከው በከፋ የሚያደርጉትን ጉብኝት ፈጽመውዋል ።

በኢሉባቦር

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ምበኢሉባቦር ሀገረስብከት ካሉት አውራጃዎች አንዱ የቡኖ አውራጃ የሆነው በደሌ ከተማ በ፫ ሰዓት ተኩል ገደማ እንደደረሱ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስና ቀሲስ ብርሃኑ መንገሻ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የአውራጃው አስተዳዳሪ ጓድ አጥናፉ ተሾመ ከከተማው አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ወጥተው በክብር ተቀበሉአቸው ቅዱስነታቸው በክብር ታጅበው ከከተማው እንደደረሱ የከተማው ነዋሪ ሕዝብ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የመንፈሳውያን ወጣቶች ማኅበራት የኢትዮጵያን ባንዲራ እያውለበለቡ በሆታና በዕልልታ በይባቤና በዝማሬ ተቀበሉአቸው ቅዱስነታቸውም ወደ ቅ/ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በማምራት ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው ሥፍራ እንደተገኙ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ እንኳን ደህና መጡልን በማለት በኢሉባቦር ምእመናን ስም አጭር ንግግር አደረጉ ከዚህ ቀደም ብሎ ግን የአውራጃው ሰባኬ ወንጌል አባ ኃይለ ማርያም ገሠሠ የቅዱስነታቸውን ጉብኝትና በአውራጃው ስለተቋቋመው የካህናት ማሠልጠኛ በሥተንተን ንግግር አድርገዋል ከዚህ በኋላም ቅዱስ ፓትርያርኩ ቃለ ምዕዳን አሰምተው ለተሰበሰቡት ምእመናን ቡራኬ እንደሰጡ የአቀባበሉ ስነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኖ አል ።

በዚሁ ከተማ ምሳና ዕረፍት ከተደረገ በኋላ ቅዱስነታቸውም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው በሚጓዙበት ወቅት በበደሌ አካባቢ አዲስ የተቋቋመው የካህናት ማሠልጠኛ ጣቢያን እንደ በአንድ ጉብኝተዋል ይህ በዚህ እንዳበቃ ጉዞው ቀጥሎ በዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ መቱ ከተማ ገብተዋል ፤ ከከተማው አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኘው በሶርና ገባ ወንዝ አካባቢም የክፍለ ሀገሩ ም/አስተዳዳሪና ሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣኖች በክብር ተቀብለዋቸዋል ቅዱስ ፓትርያርኩ መቱ ከተማ መንበረ ጵጵስና ቅጥር ግቢ እንደደረሱ በዚያው ተሰልፎ መምጣታቸውን ሲጠባበቅ የነበረው በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ በእልልታና በሆታ በዝማሬና በልዩ ልዩ ቅኔዎች ከፍተኛ አቀባበል አድርጎላቸዋል ከዚያም ወዲያውኑ ፤ ጉዞ ወደ ጎሬ ከተማ ተደርጎ በአሥራሁለት ሰዓት ተኩል ሲገቡ የአውራጃው አስተዳዳሪ የፖሊስና የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንዲሁም በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የከተማው ነዋሪዎችና ካህናት ወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ከፍተኛ ድምቀት የተመላበት አቀባበል አድርጎላቸዋል በዚህ ወቅት ቀሲስ ብርሃኑ የቅዱስነታቸውን ጉብኝት አስመልክተው ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል ሆኖም ሰዓቱ መሸት ብሎ ስለነበር ቅዱስነታቸው ቃለ ምእዳንና ቡራኬ የሚሰጡበት እሁድ





ቅዱስነታቸው በጅማ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው መምጣታቸውን ሲጠባበቁ ለነበሩት አባታዊ ምክርና ትምህርት ሲሰጡ ።



www.ethiopianorthodox.org

ጥዋት እንዲሆን ተወስኖ የአቀባበሉ በነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኖአል ቅዱስነታቸውም ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ወደተዘጋጀ ላቸውማረፊያ ሄደዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም በቅ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ሥርዓት ጸሎት አድርሰዋል በዕለቱ ለተገኙት ምእመናን አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል በዚሁ ዕለት ጎሮሮ አካባቢ የሚገኘውን የመንግሥት የሻይ ቅጠል ተክልና በጎሬ ከተማ ክልል የሚገኘው የቅ/ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ን ጎብኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም እሁድ በጎሬ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተዋል ሥር ዓተ ቅዳሴውም በቅዱስነታቸው መሪነት በብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ ሠራዒነት ተከናውኖአል በዚሁ ወቅት የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ከቅዱስነታቸው ቃለ ምዕዳንና ቡራኬ ለማግኘት በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ ተሰብስቦአል በዚሁ ሰዓት የደብሩአስ ተዳዳሪ ቆሞስ አባወልደ ሥላሴ ንጉሤ ንግግር አድርገዋል ቀጥሎም ቅዱስነታቸው ቃለምዕ ዳን አሰምተው ቡራኬ ሰጥተዋል ፤ ከዚያም በደብሩ የሚገኙትን ድርጅቶች በደብሩ ፣ አስተዳዳሪ በቆሞስ አባ ወ/ሥላሴ ንጉሤ አማካይነት እየተዘዋወሩ ተመልክተዋል ። የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርንም በአውራ ጃው ሰባኬ ወንጌል በመምህር ገብረ ወልድ ሀብተ ማርያም አማካይነት ጎብኝተዋል ለወ ጣቶቹና በጎብኝቱ ወቅት ለተገኙት ምእ መናንም ስነሥቅለት ያለበትን መስቀል ሰጥተዋቸዋል ፤ ጉብኝቱ በዚህ አኳኋን እንዳበቃ ወደ መቱ አምርተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በመቱ ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ወደ መቱ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሄደው የመሠረተ ድንጋይ አኑረዋል ፤ የመሠረት ድንጋይ ማኖር ስነ ሥርዓት እንዳለቀ ቅዱስ ፓትርያርኩ በዕለቱ ለተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያኑ መሠረት ማኖ ሩ ሣይሆን የሚጠቅመው ተሠርቶ ሲገለገል በት ማየት ስለሆነ ሠርታችሁ ለማየት ያብቃን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ሥራው ተጠናቅቆ ታቦቱ ሲገባም በመካከላችሁ ተገኝተን እንባርክላችኋለን ስለ ሥራውም በጠቅላይ ቤተ ክህነት በኩል የገንዘብ ርዳታ እናደርግላችኋለን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን በማለት ምእዳንና ምክር ካሰሙ በኋላ ቡራኬ ሰጥተው በሄዱ በት አኳኋን ተመልሰዋል ።


ቅ/ፓትርያርኩተመልሰውጅማከተማሲገቡ የሀገረስብከቱወጣቶችመንፈሳዊ ማኅበር በድ ጋሚአቀባበል አድርገውላቸዋል ቅዱስነታ ቸውም ሥነ ስቅለት ያለበትን መስቀል ለእያ ንዳንዳቸው ሰጥተው ወደማረፊያቸው ገብ ተዋል አዳር በጅማ ሆኖ የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በሰላም ከመንበራቸው ገብተዋል ።

## ወለጋ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከየካቲት ፲፪ እስከ የካቲት ፳፩ ቀን ወለጋ ንና አውራጃዎቿን ጎብኝተው ተመልሰዋል ።

ቅዱስነታቸው ብፁዓን ጳጳሳትንና የቤተ ክህነት ሹማምንትን እንዲሁም ጋዜጠኞ ችን አስከትለው ከላይ በተጠቀሰው ቀን ከአዲስ አበባ ተነሥተው ነቀምቴ አው ራጃ ሰሬስቡ ከተማ ሲደርሱ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የከተማው ሕዝብና ልብሰ ተክ ህኖ የለበሱ ካህናት ከከተማው መግቢያ በር እስከቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ድረስ ግራና ቀኝ በመሰለፍ ደማቅ የሆነ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። በዚሁም ወቅት ቅዱስ ፓትርያርኩ ለተሰበሰቡት ምእመናን ልጆ





ፓትርያርክ ተክለ ሃይማኖት ወለጋን ለመጎብኘት ለቀምት ከተማ እንደደረሱ የከተማው ሕዝብ ልባዊ አቀባበል ሲያደርግላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org



ፓትርያርኩ በአሶሳ ሠፈራ ጣቢያ አዲስ በተሠራው የቅ/ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ለተሰበ በሰው ሕዝብ አባታዊ ትምህርት ሲሰጡ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የግምቢን ከተማ በጐበኙበት ወቅት የከተማው ሕዝብ ልባዊ አቀባበል ሲያደርግላቸው ።



ቻቸው በሃይማኖታቸው እንዲጠነክሩ አሳ ስበው ቡራኬም ሰጥተው ጉዞአቸውን ወደ ነቀምቴ አመሩ ። ቀደም ብሎ ግን ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ የሀገረ ስብከቱ ሠራተኞችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች በባኮ ከተማ ተገኝተው ተቀ ብለዋቸዋል ።

ፓትርያርክ ተክለ ሃይማኖት ነቀምቴ ከተ ማ ሲገቡ ከከተማው በር እስከ ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን ድረስ የተሠለፈው ሕዝበ ክርስቲያን የቅዱስነታቸው መምጣት እጅግ ስላስደሰተው የተሰማው ደስታ በሆታና በዕልልታ ገልጾታል ።

ቅዱስነታቸውም ወደ ቤተ መቅደሱ ገብ ተው የህሊና ጸሎት አድርሰው ወደተመደ በላቸው ሥፍራ እንደወጡ ስለተደረገላቸው ልባዊ አቀባበል አመስግነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪ ክና የኢትዮጵያ ነጻነት ለዘለዓለም ተጣ ብቆ የኖረ እንደመሆኑ መጠን ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ መጠበቅና ማስጠበቅ እንዳለበት አስገንዝበዋል ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በአሦሳ ሠፈራ ጣቢያ የሚገኙት ወዛደሮች ቤ/ክርስቲያን ካልተሠራልን ለመኖር አን ችልም በማለት በቀረቡላቸው አቤቱታ ፣ መሠረት ከልማት ኮሚሽን ብር ፴ሺ ብር (ሠላሳ ሺህ ብር ) ወጭ ሆኖ እንዲሠራ ስለፈቀድዱላቸው በዚሁ ወጭ ፲፩ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተው በአገልግሎት ሲገኙ ፤ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በመሠራት ላይ ይገኛሉ ። እንዲሁም በአን ገር ይተን ሠፈራ ጣቢያም አራት አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተው በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ። ቅዱስነታቸው ወለጋን በጎበኙበት ወቅት ከ፳፱ባልበለጡ አብያተ ክርስቲያናት በመገኘት አባታዊ ምክርና ትምህርት በመስጠት ቡራኬም በማስተላለፍ የሚፈ ለግባቸውን አባታዊ ግዳጅ ፈጽመዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ተክለ ሃይ ማኖት በመንዲ ፤ በአሦሳ ፤ በነጆ ፤ በጊምቢ፤ በኖሌካባና ፤ በአንገርይተን ፤ በዚሁ ተመ ሳሳይ ጉብኝት አድርገው በሄዱበት አኳኋን ወደመንበረ ካናቸው ተመልሰዋል ።

የዜናው አቅራቢ ገብረ ክርስቶስ ኃ/ ማርያም



www.ethiopianorthodox.org

# ያችን ዕለት ያችን ሰዓት

ደብረ ዘይት ማለት በኢየሩሳሌም ምሥራቅ ያለ ተራራ ነው ። ዘይት ማለት ወይራ ማለት ነው በአጠቃላይ እንደወይራና የመሳሰሉት ቅብዓትነት ያላቸው ዛፎችና ዕፀዋት የሚበቅሉበት ቦታ ማለት ነው ። ደብረ ዘይት እየተባለ በሚጠራው ቦታ ጌታ ይጸልይበት ለትሩፋት ቆይታ ያደርግበት እንደነበር በሉቃስ ወንጌል ቀን በምኲራብ ሲያስተምር እየዋለ ሌሊት ኤሌዎን በሚባል በደብረ ዘይት ሲጸልይ ያድር ነበር በማለት ይታወቃል።ጌታ ጸሎት የሚያደርግበት በደብረ ዘይት ብቻ ሳይሆን በጌቴሴማኒም እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ስለጸሎት ወንዙን ተሻግሮ ዛፉን አልፎ ወዳለው ዱር ገባ ይልና የተክል ቦታ መሆኑንም ሲያመለክት ወቦ ህየ ዓጸደ ሐምል በማለቱ ጌቴሴማኒም መሆኑን ያረጋግጣል ።

ደብረ ዘይት በኢየሩሳሌም ውስጥ መሆኑንና ደብረ ዘይትና ጌቴሴማኒ ደብረ ጽዮን በአንድ አካባቢ ቅርብ ለቅርብም እንደሆኑ ታሪኩ ከማመልከቱም ሌላ ከቦታውም ደርሰውና ጎብኝተው ከመጡ ከአንዳንዱ ሰዎች ለመረዳት ይቻላል (ታዲያ ጌታ የሚመጣበትበዕለተ እሁድስለሆነ የምጽአቱ መታሰቢያ ደግሞም በቦታው ደብረ ዘይት ተባለ ጌታ በዚሁ በዕለተ ዕሁድ ብዙ ሥራ የሠራበት ስለሆነ ዕለተ ጠቢባን ይለዋልን? ። ሥላሴ ጠቢባን ከዕለታት ሁሉ መርጠው አስቀድመው ዓለምን የፈጠሩ በት ዕለት ነው ይኸውም ዕለተ እሁድ ነው በዚሁ ዕለት ጌታ ተጸንሶበታል ተነሥቶበታል ። በኋላም ዓለምን ያሳልፍበታል ይኸውም ዓለም የሚያልፍበት ደብረ ዘይት ነው ። ለመሆኑም ማስረጃው «ይህ ኢየሱስ በደመና ወደሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት እንደዚሁ በደመና ይመለሳል በማለቱ ይታወቃል ። ግብ ሐ ፩/፲፩ ።

መጋቢት ፳፱ በ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም በከበበ ትስብዕት እንደመጣ እንዲሁ ለፍርድ በዚሁ ዕለት የሚመጣ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ሲያረጋግጡ በከመ ወረደ ለአድኅኖ ከማሁ ይመጽእ ለኰንኖ በማለት ጠቁመዋል ።

ይሁን እንጂ ዋናው ፍሬ ነገር ደብረ ዘይት ለሐዋርያት ነገረ ምጽአትን የገለጸበት ወደ ሰማያዊ ክብሩ በሥጋ ያረገበት ኋላም ዓለምን በሚያሳልፍበት ጊዜ የብርሃን ዙፋን የሚዘረጋበትና ለሙታንናሕያዋንን ንዑና ሑሩ በማለት ፍርድ የሚሰጥበት መለኮታዊ ዓውደ ግርማ እንደሆነ በምስክርነት ግርምት ዓውድ በማለት ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረውበት ይገኛሉ ።

አምላክ ወልደ አምላክ ሰው ሆኖ በአስተማረበት ጊዜ ናሁ ይትኀደግለክሙ ቤትክሙ በድወ እነሆ ቤተ መቅደስ ትፈርሳለች ባላቸው ጊዜ ሐዋርያት የሕንጻውን ውበት አይተው እንዲህ ሲያምር ይፈርሳል ትላለህን ብለው ሲጠይቁት ለዚህ ምሳሌ ሰጥቶ ይህንን በማስደነቅ ታያላችሁን ደንጊያ በድንጊያ ላይ ተነባብሮ የማይፈርስ ሆኖ (ሳይፈርስ) አይቀርም በማለት ረቂቅ ምሥጢር ገልጾላቸዋል ። ይህንንም ከሐዋርያት ጋር እየተነጋገረ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ወደ ደብረ ዘይት ሔዶ ለጊዜው ከደብረ ዘይትም ተቀመጠ፤ በዚህን ጊዜ ቤተ መቅደስ ይፈርሳል እያለ በልዩ ልዩ ምሳሌ የነገራቸው ሐዋርያት ምሥጢሩ ከብዶአቸው ነገሩ ከንክኗቸው ነበርና ።

ይልቁንም ባለሟሎቹ ቅዱስ ጴጥሮስና የዘብዴዎስ ልጆች እነያዕቆብና ዮሐንስ እንድርያስን ጨምረው ለየት በማለት ወደ ጌታ ቀርበው ቤተ መቅደስ መቼ እንደሚፈርስ ዕለተ ምጽአትም ምንጊዜ እንደሚሆንና ምልክቱስ ምን እንደሆን ግለጽልን በማለት ጠይቀውታል ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በኔ ስም ይነሣሉ እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ መምህራንን የሚያሳብሉ ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ ፤ ብዙ ሰዎችንም ያስታሉ በዚያን ጊዜ ብዙ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ ከእግዚአብሔር ሥርዓት የሰውን ሥርዓት በመጠበቅ ልጅ አባቱን አባት ልጁን ወንድም ወንድሙን ሳይፈራ ጨክኖ ለሕማም ለመከራ ለሥቃይ ለሞት አሳልፎ ይሰጣል ፤ ትትሴኩስ ፍቅር ይላል ከኃጢአት ብዛት የተነሣ ፍቅር ከሰዎች ትጐድላለች ፤ ጨርሳም ትጠፋለች ካለ በኋላ ስለመከራው ጽናት እንዴትም እንደሆነ ሲገልጽ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ተደርጎ የማያውቅ ከንግዲህ ወዲህም የማይደረግ ጸዋትወ መከራ ያን ጊዜ ይደረጋል።ቀኑስ ባያጥር ኖሮ ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ ከመከራ ከክህደት ባልዳነም ነበር ፤ በእንተ ኅሩያኒሁ ይላል፣ነገር ግን ስለምእመናኑ ስለ ቅዱሳኑ ቀኑ ያጥራል በማለት ገልጾላቸዋል ።

በደብረ ዘይት የክርስቶስ የመምጣቱ ምልክት ሐሳዌ መሢህ እንደሆነ ሁሉ ፤ ለሐሳዌ መሢህም የመምጣቱ ምልክት የሐሰተኞች መምህራን መነሣት እንደሆነ ማቴዎስ ፳፬ ቁጥር ፳፬ ላይ ሰውን ያስቱ ዘንድ በምትሐት አስደናቂ ተአምራት ያደርጋሉ ይላል፣ቢልም ቅሉ የኢአማኒ ተአምር በእግዚአብሔር መንግሥት ተቀባይነት እንደሌለው እስመ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት ኢይክል ያድኅን እምኵነኔ ገሃነም ከማለቱም ሌላ ወይገብሩ ተአምራተ ወመንክራተ ዓበይተ ለአስህቶ ሰውን ለማሳት በሕዝብ ፊት ተአምራት ያደርጋሉ ። ሲል በየጊዜው በሚነሡት ነቢያተ ሐሰት ጭምር ጠቁሞ ይገኛል ።

ሐሳዌ መሲህ ፫ ዓመት ተመንፈቅ በድምር የፈለገውን ለመፈጸም ምትሐታዊ ሥልጣን የተሰጠው እንደመሆኑ በምትሐቱ አናምንብህም የሚሉ ምእመናንን በሰይፍ ያስፈጃቸዋል፤ምእመናን የተባሉም እነኤልያስናእነ ሄኖክ እነ አቡነ አረጋዊ የመሳሰሉት ሁሉ ማለት እስከ ምጽአት በሕይወት እንደ ብሔረ ብፁዓን ባሉ በተወሰኑ ቦታዎች የሚኖሩና ያን ጊዜ ለሰማዕትነት የሚገለፁ ናቸው ማለት ነው። ፪ቱ አልሕምት (ዕፀ ዘይት ) የተባሉ ሄኖክና ኤልያስ በሐሣዌ መሢሕ ከተማ ገብተው የሚያደርገውን ተአምራት ሁሉ በምትሐት እንደሆነ በዓለሙ ዘንድ ቁልጭ አድርገው ያጋልጡታል ። በዮሐንስ ወንጌል ወሶበ ይነብብ ሐሰተ እምዚአሁ ይነብብ እስመ ሐሳዊ ውእቱ ወአቡሃ ለሐሰት እንደአለው ሐሰትን ውሸትን በተናገረና በሠራ ጊዜ ከልቡ አንቅቶና ፈልስፎ የሚያደርግ ሐሰተኛ የሐሰት አባቷ የክህደት መሠረቷና መዝገቧ የዲያብሎስ ፍጹም የግብር ልጁ መሆኑን ሳያፍሩ ይመሰክሩበታል ። ስለዚህ ሐሣዌ መሢሕ ተናዶ በሰይፍ ያስፈጃቸዋል ። በዚህም ጊዜ በሐሣዌ መሢሕ አስደንጋጭ ገጽታና በግርማ ሰይፉ ብልጭታ ሳይርበደበዱና ሳይሰቀቁ ያለፍርሃት ሐዋርያው በ፪ኛ ቆሮንቶስ በም ፩ ቁ ፮ በተናገረው መሠረት) እንዲህ ይላሉ እኛ በሁሉ ይከፋናል ነገር ግን አንጨነቅም ፣ መከራ እንቀበላለን ነገር ግን ተስፋ አንቆርጥም፤እንሰደዳለን ነገር ግን አንጠላም፤እንወድቃለን ነገር ግንአንጠፋም፤

ሁል ጊዜ የክርስቶስንም ሞት በሥጋችን እንሸከማለን ፣ የክርስቶስ ሕይወት በሥጋችን ይገለጣል ፣ እኛም ሕያዋን ሆነን ሳለን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለሞት ተሰጥተናል ፣ በዚህም በሚሞተው ሥጋችን የክርስቶስ ሕይወት ይገለጣል ፤ እንግዲህ ሞት



www.ethiopianorthodox.org

ምንም በላያችን በርትቶ ቢሆን ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛንም ያስነሣናል ።

ስለዚህ አፍኣዊ ሥጋችን ቢጠፋ ውሳጣዊው ሰውነታችን ዕለት በዕለት ይታደሳልና አናዝንም ፥ የዚህ ዘመን መከራ ምንም አላፊና ቀላል ቢሆን ለዘለዓለም ፍጻሜ የሌለው እጅግ ታላቅ ክብር ይሰጠናል የማይታወቀውን ሰማያዊ ተስፋ እንጂ ይህንን የሚታየውን አንመለከትም የሚታየው ይህ ዓለም የዛሬ ነውና ያልፋል ፤ የማይታየው ግን የዘለዓለም ነውና አያልፍም ፥ እያሉ በታላቁ ኃይል ሰማዕትነት ተቀብለው ይሞታሉ ፥ እስከ ፫ ቀን በድናቸው እንዳይቀበር ሐሣዊ መሢሕ ይከለክላል በሦስተኛው ቀን ይነሣሉ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችንን ለመቀበል ወደአየር እንወጣለን እንዳለው በደመና ወደ አየር ተነጥቀው በሕይወት ሥጋ ያርጋሉ በማለት ታሪኩ አስፋፍቶ ያስረዳል ።

ከዚህ በኋላ ምጽአተ ክርስቶስ ሰማይና ምድርን በመብረቅ እያረሰ ወደደብረ ዘይት ያመራል ወይእተ አሚረ ያስተርኢ ትእምርቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ውስተ ሰማይ ይላል ያን ጊዜ የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ምልክቱ በሰማይ ይታያል ለናንተ ስል ልዩ ልዩ መከራ ተቀብዬ እንዲህ ሁኜ ተሰቀልሁላችሁ እናንተስ ምን ወረታ መለሳችሁልኝለማለት አሰረ ርግዘቱን አሰረ ቅንዋቱን፤ እሥራቱን ፤ ግርፋቱን ሳያጠፋ በዕለተ ዓርብ እንደተፈጸመው ሆኖ በሔሮድስ የተፈጁትን ሕጻናት አስከትሎ በዕልፍ አዕላፋት መላእክት ታጅቦ እጁን እግሩን በቀኖት የቸነገሩትን በጦር ጎኑን የወጉትን ያዩ ዘንድ አላቸው እንደተባለው ያን ጊዜ ሰቃልያኑ እያዩት መግቢያ እስኪያጡ ፥ እያፈሩት ይመጣል በማለት ይናገራል።ይህም እንደሚሆን ቀደም ብሎ ለአባ ጰኩሚስ ተገልጾለታል። አባ ጰኩሚስ ሲሰግድ ወዙ

ወርዶ መሬቱን ጭቃ አደረገው ወዲያው ጌታ ተገለጸለት አንተን አገኝ ብዬ እንዲህ ሁኜ እደክማለሁ አለው እኔም እንጂ ለአንተ ብየ እንዲህ ሁኜ ተሰቅያለሁ ብሎ በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሁኖ ጐኑ እንደተወጋ ደሙ እንደፈሰሰ ሆኖ ታይቶታል ።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በዚያን ጊዜ ሰማይና ምድር አልፈው ቀደም በደብረ ዘይት መለኮታዊ ዙፋን ይዘረጋል ሙታን ይነሣሉ ታዲያ የተነሣንበትን ዓላማ ሳንዘነጋ የምጽአት አፈጻጸም ትንሣኤ በመሆኑ ስለትንሣኤ በመጠኑም ቢሆን ሳናወሳ አናልፍምና ስለ ትንሣኤ ቅዱስ ጳውሎስ ሲጽፍ መጀመሪያ ክርስቶስ ተነሣ ይልና ክርሱ በኋላ ያመኑበት ጻድቃን በዳግም ምጽአት መነሣታቸውንና የመጨረሻው ቀን ትንሣኤ ዘጉባኤ ሆኖ ገዥዎች በተሻሩ ጊዜ ነገሥታትም መንግሥታቸውን መልሰው ለእግዚአብሔር አብ በሰጡ ጊዜ መሆኑንና አነሣሡም በየማዕረግ በየማዕርጉ መሆኑን ገልጾታል ። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህም ብቻ ሳይገታ ስለትንሣኤ አስፋፍቶ ሲጽፍ ጌታችን በመላእክት አለቃ ድምፅና በዕልልታ በመልከትም ድምፅ ከሰማይ ይወርዳል እኛም የሞቱትን አንቀድማቸውምና እነዚያ አስቀድመው የተነሡትን ተከትለን ጌታችንን ለመቀበል በደመና ወደ አየር እንወጣለን ይላል ፤ ፩ ተሰሎ፡፲፫ ፲፰ ከዚህም ሌላ ዮሐንስ በራእዩ ትንሣኤ ፪ ጊዜ መሆኑን እንዲህ ሲል ጽፎታል ።

ስለ ኢየሱስ ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል የሞቱትን ነፍሳት አየሁ ለአርዌውም ያልሰገዱ የሥልኩንም ጽሕፈት በግንባራቸው ያልጻፉ በእጃቸውም ያልተከተቡ እርሳቸው አስትድመው ይነሣሉ ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ ወባዕዳንሰ ምዉታን ይላል ሌሎች ሙታን ግን ሺህ ዓመት እስኪፈጸም አይነሡም የመጀመሪያይቱ ይህች ናት ከመጀመሪያይቱ ትንሣኤ ዕድል



ያለው ብፁዕ ወቅዱስም ነው በነዚህ ላይ ፪ኛው ሞት ሥልጣን የለውም ነገር ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ሁነው ይኖራሉ ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ ፥ ራዕ ፳፮ በማለት አሻሚ በሌለው ማስረጃ ገልጾታል ።

ያችን ዕለት ያችን ሰዓት የማያውቃት የለምና ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ባልጠረጠራችሁት ዕለት ባላወቃችሁት ሰዓት እንዲመጣ ስለማታውቁ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ በማለት የተናገረውን አምላካዊ ማስጠንቀቂያ በማሰብ ይችን ዕለት ደብረ ዘይትንና ከዚህም ወዲህ ዕለተ ሞትን ሁሉ በፍርሃት ይጠባበቃል እንዲያውም ድልዋኒከሙ በንስሐ ነጽታችሁ ሀልዉ ያለው ከኃጢአት በጾም በጸሎት ተጸምዳችሁ ሥጋ ወደሙን በመቀበል ክርስቶስን ለብሳችሁ ከክርስቶስ ጋር ነግሣችሁ እንድትኖሩ የክርስቲያን ዓርማ የሆነው መስቀለ ሞቱን በመሸከም ተሰልፋችሁ ቆዩኝ ያለውን አንዳንድ ግብዞች ዘንግተው በዓመት በዓመቱ ደብረ ዘይት በሆነ ቍጥር ሰማይና ምድር ያልፋል እያሉ ሲረብሹ ሲያሸብሩ እንደሚውሉ ሐሰት አይባልም እንዲያውም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ ወርሁ ወርኀ መጋቢት ዕለቱ ዕለተ እሁድ ሰዓቱ ዓሥር ሰዓት መሆኑን ጠቁመው ይገኛሉ ።

ያም ሆነ ይህ ክርስቲያናዊ ግዳጃችን ከኃጢአት በንስሐ ነጽተን ሥጋ ወደሙ ተቀብለን መስቀለ ሞቱን ተሸክመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት በመጣ ጊዜ ተሰልፈን ለመቀበል እንድንችል መሆን ነው

ከይቁም ግዛው



www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት

# ሰሙነ ሕማማት ፤

ከሆሣዕና በኋላ ያለው ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ተብሎ ይጠራል ፤ የቃሉ ትርጓሜ «ሰሙን» ማለት ስምንት ማለት ሲሆን «ሕማማት» የሚለው ቃል ደግሞ ሕመም ያለውን ሕማማት በማለት አብዝቶ ይናገራል ፤ በጠቅላላው ቃሉ ሲተረጐም የመከራ ሳምንት ማለት ሲሆን ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ግን የተቀደሰ ሳምንት ብለው ይጠሩታል ፤ ይህ ሳምንት የመከራ ሳምንት ተብሎ ሊሠየም የቻለው እውነተኛው አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጅ ሲል ብዙ ፀዋትወ መከራዎችን የተቀበለበት ሳምንት በመሆኑ ነው ።

በዚህ ሣምንት ውስጥ የሚነበበው መጽሐፍ ከብሉያትና ከሐዲሳት ከሊቃውንትና ከድርሳናት የተዘጋጀ እንደመሆኑ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበላቸውን ፀዋትወ መከራዎች በዝርዝር ያስተምራል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዚህ ዓለም መጥቶ ብዙ ፀዋትወ መከራን በመበቀል ለሰው ልጅ ቤዛ መሆኑን አስቀድሞው በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኙ ትንቢት ከተናገሩት ነቢያቶች መካከል በተለይ ነቢዩ ኢሳይያስ ይህንን በማስለመከት ምስክርነታችንን ማን ይቀበለዋል የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል? በፊቱ እንደቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደሥር አድጎአል ፤ መልክና ውበት የለውም በዚያም ጊዜ እወደው ዘንድ ደምግባት የለውም ፤ የተናቀ ከሰውም የተጠላ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው ፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሠውርበት የተናቀ ነው ፤ እኛም አላከበርነውም ፤ በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል ፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ ፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን - - - ተጨነቀ ተሠቃየም አፋንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፋን አልከፈተም - - - - በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር ሲል ተናግሯአል ኢሳ ፤ ፶፫ ቍ ፩—፲ ።

ይህ የነቢዩ ትንቢት በእውነት ያለ ሐሠት በትክክል የተፈጸመው በዚሁ በሰሙነ ሕማማት ነው ፤ ሰሙነ ሕማማት በሩቅ የነበሩትን ቀርቶ እሱ በዋለበት እየዋሉ እሱ ባደረበት እያደሩ ትምህርቱን በቅርብ ሆነው በየዕለቱ ይመለከቱ የነበሩ ሐዋርያትን እንኳን ሳይቀር በከፍተኛ ትዝብት ላይ የጣለ ሣምንት ነው ማቴ ፤ ም ፤ ፳፮ ፤ ቍ ፤ ፴፬ ፤ ፵፯ ፤ ይመልከቱ ።

ምክንያቱም ከነቢዩ ቃል እንደ ምንረዳው ሰው ፊቱን እንደሚሠውርበት የተናቀ ነው። እኛም አላከበርነውም ፤ ሲል የተናገረው ቃል በሰሙነ ሕማማት ብዙዎቹ ፊታቸውን እንዲያዞሩ አድርጓቸዋልና ሌላው ቀርቶ ፀሐይና ጨረቃ እንኳን ሳይቀሩ ፊታቸውን እንዲያዞሩ ተገደዋል ።

ስለዚህ ነው ሰሙነ ሕማማት ብዙዎቹን በከፍተኛ ትዝብት ላይ ጥሎአቸዋል ለማለት ያስቻለን ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰሙነ ሕማማት የተቀበላቸው ፀዋትወ መከራዎች ብዙዎች መሆናቸውን የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተለያዩ ቁጥሮችን ይሰጣሉ ፤ ይኸውም አንዳንድ ሊቃውንት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል ፫፻፲፰ ነው ብለው ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ፮ሺ፮፻፷፮ ነው ብለው ያስተምራሉ ፤ ሆኖም በቅዱስ ወንጌል ላይ ተጽፎ እንደምናገኘው ከሆነ ዋና ዋናዎቹ ፲፫ ሆነው እናገኛቸዋለን ።

እነሱም ፤

ሀ/ አክሊለ ሶክ ( የሾህ አክሊል )
ለ/ ተኰርዖተ ርእስ (ኢሳ ፤ ፩ ፤ ቁ፭
ሐ/ ተጸፍአ መልታሕት (ኢሳ ፤ ፶ ፤ ቁ ፤ ፮)
መ/ ተወክፎ ምራቅ (ኢሳ ፶ ፤ ቁ ፤ ፮)
ሠ/ ሰትየ ሐሞት (መዝ ፤ ፷፰ ፤ ቍ ፤ ፳፩)
ረ/ ተአሥሮ ድኅሪት
ሰ/ ተቀሥፎ ዘባን ፤(ኢሳ ፤ ፶ ፤ ቁ ፤ ፮)
ሸ/ ፀዊረ መስቀል
ቀ/ ሐምስቱ ቅንዋት እነሱም ሲዘረዘሩ ሁለቱ እጆቹ ለየራሳቸው ፤ ሁለቱ እግሮቹ ለየራሳቸው ሲቆጠሩ በአንድነት አራት ይሆኑና አምስተኛው የጎኑ በጦር መወጋት ይሆናል ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ሊፈጸምበት የቻለው ሲሰርቅና ሲቀማ ወይም በአፉ ሐሰት ሲናገር ተገኝቶ ሳይሆን አንደኛ ትንቢቱ እንዲፈጸም ግድ በመሆኑ ፤ ሁለተኛ ለአዳም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ሞቼና ተነሥቼ አድንሀለሁ ሲል የተናገረውን ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ሲል ነው ፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ነቢያት የተነበዩት ትንቢት እሱም የገባው ቃል ኪዳን ከንቱ ሆኖ በቀረነበርና

በመሠረቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት ከተወለደበት ዕለትና ዓመት ጀምሮ ወይቤ ተፈጸመ ኵሉ ብሎ ነፍሱን ከሥጋው እስከለየበት ቀን ድረስ የነበሩትን የሕይወት ዘመናቱን ወደ ኋላ መለስ ብለን በዓይነ ሕሊና ስንሙለከታቸው ለእኛ ሕይወትና ድኅነት ሆነው ሲገኙ ለተከታዮቹና ለእናቱ ግን ጭንቀትና ሰቀቀን መሆናቸውን ከትዱላት መጻሕፍት ለመረዳት እንችላለን ። ማቴ ም ፪ ፤ ቁ ፤ ፲፫—፲፰ ሉቃ ም ፪ ቁ ፴፬ —፴፯ ማቴ ም ፬ ፤ ቁ ፤ ፩—፲፩ ፤ ም ፤ ፲፩ ፤ ቁ ፤ ፲፮—፳ ፤ ሉቃ ም ፤ ፳፪ ፤ ፴፱—፶፫ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሕማምና ለሞት አሳልፈው ከሰጡት አይሁዶች መካከል ጥቂቶቹ ፤

ሀ/ ፈሪሳውያን
ለ/ ሰዱቃውያን
ሐ/ ጸሐፍት የተሰኙት ናቸው ።

እነዚህ ሦስት ክፍሎች የስም ልዩነት ያላቸውን ያህል የእምነትና የምግባርም ልዩነቶች ያሏቸው ለመሆኑ በሐዲስ ኪዳን በሠፊው ተጽፎ እናገኘዋለን ።

ስለዚህ የእያንዳንዳቸው የሃይማኖትና የምግባር ልዩነትም ሆነ ይዘት እንዴት እንደሆነ ለመረዳት ይቻል ዘንድ ስለ ፈሪሣውያን ሁኔታ በቅድሚያ እንመረምራለን ።

## ፈሪሳውያን

ፈሪሳውያን የሚለው ቃል ብዛትን የሚያመለክት ሲሆን በነጠላው ፈሪሳዊ ይላል የቃሉ ትርጓሜም የተለየ ማለት እንደሆነ ታሪክ ይናገራል ፤ ይኸውም ከዓለማዊ ደስታና ከከፉ ነገር ሁሉ የራቁ የአሪትን ሕግ ከፍ ባለ ጥንቃቄ የሚከተሉ የአይሁድን ሃይማኖትና ፖለቲካ በጥብቅ የሚደግፉ ነበሩ ፤ የፖለቲካ ሰዎች እንደመሆናቸውም የእስራኤል ሕዝብ ለወደፊቱ ስለሚያጋጥመው ታላቅ ምድራዊ ግዞት ያስቡና ከባዕድ ገዥዎች ቀንበር ነፃ እንዲወጣ በመቃብያን የተመራውን የእስራኤልን ሕዝብ ያደፋፍሩ ነበር ፤ ከዳኞችና ከመኳንንቱ ከሊቃውንቶችና ከመምህራኑ አብዛኛዎቹ እነርሱ ነበሩ ፤ ይሁን እንጂ ከመንፈሳዊው ዝንባሌ ይልቅ ለአፍአዊው የሚያስቡና ራሳቸውንም





www.ethiopianorthodox.org

ከፍ ከፍ ለማድረግ በጣም የሚጥሩ እንደ ነበር በሐዲስ ኪዳን ተጽፎአል ።

ሆኖም ጌታችን በትምክህተኝነት የሚ መራውን አፍዓዊ ሥርዓታቸውን በጥብቅ በመቃወም እናንተ ግብዞች በማለት ደጋ ግሞ ወቅሶአቸዋል ። ሉቃ ፤ ፲፩ ፤ ፴፯—፵፬። ማቴ ፤ ፳፫ ፤ እስከ ፍጻሜው ይመልከቱ ፤ ምንም እንኳን ፈሪሳውያን አብዛኛዎቹ ግብ ዝነት ያጠቃቸው ቢሆኑም እንደነ ኒቆዲ ሞስና እንደነ ጳውሎስ ያሉ ቅን ሰዎችም ነበሩ ፤ ፈሪሳውያን ስለ መላእክት መኖር ስለ ትንሣኤ ሙታንና ከሞት በኋላ ስላለው ቅጣት በትክክል ያምናሉ የሐ ፤ ሥራ ፤ ፳፫ ፤ ቍ ፤ ፰ ።

በክርስቶስ ጊዜ የፈሪሳውያን ቍጥር ወደ ስድስት ሺህ ይደርስ እንደነበረ ሊቃውንት ይናገራሉ ፤ ሆኖም ፈሪሳውያን መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምረውን ትምህርት በጥብቅ ይቃወሙ ስለነበሩ እሱን ለመግደል ተማከሩ ዮሐ ፲፩ ቍ፤ ፵፯-፶፯ ።

## ጸ ሐ ፍ ት

የጸሐፍት ዋና ዋና ሥራዎቻቸው የሚ ከተሉት ነበሩ ፤ (ሀ) በነገሥታት ዘመን በቤተ መንግሥት አገልጋዮችና አማካሪ ዎች መሆን (፩ኛ) ዜና መዋዕል ፤ ፳፯ ።

ለ/ ጥሩ ልብስ ለብሰው የቀለም ቀንድ በወገባቸው መያዝ (ሕዝ ፤ ፱ ፤ ፪/

ሐ/ ሕገ ኦሪትንና ሌሎችንም ጽሑፎች በመጻፍ ማራባትና አብራርቶ መተርጐም (ማር ፯ ፤ ፩—፲፫) ዋነኛው ሥራቸው ነው ።

ሆኖም ጸሐፍት ሕጉ እንዳይጣስ የሽማ ግሌዎች ወግ የተባለውን ልማድ አወጡ ይህንንም በሕዝብ ጫንቃ ላይ ጫኑት ማቴ ፲፭ ፤ ፪—፯ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብዝነታቸውን አይቶ ወቅሷቸ ዋል ፤ ማቴ ፤ ፳፫ ፤ ፩-፴፭ በዚህ ምክንያት ጸሐፍት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንና ሐዋርያቱን በጥብቅ ይቃወሟቸው ነበር ፤ (ማቴ ፳፮ ፶፯ ። የሐ. ሥ ፤ ፬፤፩-፭ ።

## ሰ ዱ ቃ ው ያ ን

የሰዱቃውያን የእምነት ድርጅት የተቋ ቋመው እንደፈሪሳውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው ሰዱቃውያን የሚለውም ቃል የተወረሰው በዳዊትና በሰሎሞን ዘመነ መን ግሥት ሊቀ ካህናት ከነበረው ከሳዶቅ ነው ፤ ፪ኛ ሳሙኤል ፰ ቍ ፲፯. ፲፭-፳፬ ) ሰዱ ቃውያን ከአይሁድ እምነት ውስጥ ከማይ ቀበሏቸው ጥቂቶቹ (ሀ) ሰው ከሞተ በኋላ ጽድቅም ሆነ ኩነኔ የለበትም

(ለ) ትንሣኤ ሙታን የለም ከማለታ ቸውም በስተቀር የመላእክትና የመናፍስ ትንም መኖር ፈጽሞ አይቀበሉም ፤ (ማቴ ፳፪ ፤ ፳፫ — ፴፫ ። ዮሐ ፤ ፳፫ ፤ ፰ ። ሰዱ ቃውያን ፈሪሳውያንን በመቃወም የሚቀ በሉት የሙሴን ሕግ ብቻ እንጂ ተጨማሪ ውን ወግ አይቀበሉም ነበር ፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ ያስተምር በነበረበት ዘመን የአይሁድ ሊቃነ ካህናት የነበሩት ሐና ቀያፋ ከሰዱ ቃውያን ወገን ነበሩ ፤ ሐና ቀያፋ የአይሁድ ሊቃነ ካህናት በመሆን በፍልስጥኤም ውስጥ ከፍ ያለ ሥልጣን ነበራቸው ፤ ለምሳሌ ሊቀ ካህናቱ ሐና በሥልጣን ላይ ከ፮—፲፭ ዓ/ም ሲቆይ ቀያፋ ደግሞ የሊቀ ካህናትነ ቱን ሥልጣን ተረክቦ እስከ ፴፮ ዓ/ም ድረስ ሠርቷል ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመወንጀሉና በማሰቀሉ በኩል ለነበረው ሕገ ወጥ ተግባር ሁለቱም በግንባር ቀደ ምትነት ተካፋይ ነበሩ ፤ (ዮሐ ፲፩ ፵፱ ፤ ፲፰፤ ፲፰ ፤ ፲፫) ።



## አ ን ባ ብ ያ ን

ሰሙነ ሕማማት የሚለውን ርእስ ይዘነ ከተነሣን በኋላ ከላይ ወደተጠቀሱት ሦስት ክፍሎች ሐሳባችንን ያመራነው ለነገረ ስቅ ለቱና ሕማሙ ዋና ምክንያት ሆነው በዘ መኑ የተገኙት እነሱ ስለነበሩ ጥንተ ታሪ ኩን ለማስረዳትና ለማስተማር ስንል ነው።

ስለዚህ በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክር ስቲያን ተብለን የምንጠራው ፤ ይህንን ሣምንት የምናስበው ከሌሎች ሣምንታት የተለየ ሣምንት አድርገን ነው ፤ ምክን ያቱም ስግደት ምህላና ጸሎት በማድረግ አብዝቶ ከመብላትና ከመጠጣት ተወግደን ራስን ለቅድስና በማስገዛት ወደ ቤተ ክር ስቲያን እየሄዱ በየዕለቱ የሚነበቡትን ቅዱሳት መጻሕፍትን በመስማት ልብ ማድ ረግ የሚገባና ክርስቲያናዊ ግዴታም ስለ ሆነ ይህንን ለመፈጸም እንችል ዘንድ «ወይ ኩን ፈቃድከ» እያልን ፈጣሪያችንን እን ለምነው ።

አዘጋጅ ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳን ካሣ የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ዋ/ ኃላፊ



www.ethiopianorthodox.org

# በመስቀሉ ደም ሰላምን መሠረተ ፤

ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ቈላስይስ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ፡ ሰው ከፍጥረቱ ሁሉ የከበረ ገናና ፍጥረት መሆኑን የተረዳና ያወቀ ዲያብሎስ በቅንዓትና በምቀኝነት ባሕር ስለተዋጠ ከሚገባው በላይ እንዲመኝ ገፋፍቶ ከፈጣሪው ጋር እንዲጣላ አደረገው ።

የተመኘውን ማግኘት ይቅርና ከክብሩ እንዲዋረድና ፈጽሞ እስከመውደቅ አደረሰው በአባቶቻችንም አነጋገር እንደሚነገረው ሁሉ አተርፍ ባይ አጉዳይ ሆነ ።

ለዚህም ያደረሰው ጠባብ አስተሳሰብ አምላክነትን መመኘት ሲሆን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት የባሕርይ ገንዘቡ ነውና ሰውን ቸል ብሎ አላለፈውም ።

ረቂቁ የማይታይ የባሕርይ አምላክ ጎልቶ ታይቶ የማይዳሰሰው አምላክ በአይሁድ እጅ ጸዋትወ መከራ ተቀብሎ የማይሞተው አምላክ በለበሰው ሥጋ ተሰቅሎ ሙቶ የሚአድነው መሆኑን በትንቢታዊ አነጋገር ተስፋውን አበሠረው ።

አዳምም አምላኩ በተናገረው ቃል ብቻ እድናለሁ ብሎ የሥራ ፈት ልማድ በእእምሮው ውስጥ አልሰፈነችበትም በእእምሮው ላይ ሰፍናበት የኖረች አንብዐ ንስሓ (የንስሓ ልቅሶ) ስትሆን ሌሊትና ቀን ባለማቋረጥ ከማልቀስ በስተቀር ሌላ ሕሊና አልነበረውም አምላካችንንም መከራ ለመቀበል ያበቃችው የአዳም የንስሓ ልቅሶ እንደሆነች መጻሕፍት በየበኩላቸው ገልጸውልናል እስከ ምጽአት ድረስም ለሚነሣው ትውልድ ሁሉ ይገልጹለታል ።

የአምላካችን የተስፋ ትንቢትና የተስፋ አባባል (ቃል ኪዳን) በአዳም ብቻ ተወስኖ አልቀረም እንሆ ለአብርሃምም እንዲህ ሲል ተናግሮታል ፤ ወይቤሎ ሶበ ገባእኩ አመጽእ ኀቤከ ዐመ ከመ ዮም ወትረክብ ሣራ ወልደ ።

የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመጣለሁ ሚስትህም ሣራ ልጅን ታገኛለች ሲል ተስፋውን ነግሮታል ይሄንም የተስፋ አነጋገር ወይም ምሥጢሩን ጠለቅ አድርገን ብንመለከተው በዘመነ ሥጋዌ የሚአደርገውን እንጅ ከቶ ተመልሶ ከአብርሃም ቤት ( ድንኳን ) የሚመጣ ሆኖ አይደለም ።

ነቢያትም በየበኩላቸው አምላካዊውን ተስፋ መመሪያ በማድረግ የክርስቶስን ሰው መሆንና ዓለምን በመስቀሉ የሚዋጅ መሆኑን አስቀድመው በትንቢት ዓለምን አጐናጽፈዋት ነበር ከእነርሱም አንድ ኢሳይያስ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድን ከአበሠረ በኋላ ሞቱን አያይዞ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል ውእቱ ነሥአ ደዌነ ወፆረ ሕማመነ ።

በእውነት ደዌያችን ተቀበለ ሕመማችንም ተሸከመ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቈሰለ ስለ በደላችን ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን ብሎ በትንቢታዊ ትምህርቱ የመዳናችንን ተስፋ ስለ ነገረን በዚያን ጊዜ በዘመኑ የነበሩትም ሆነ ዛሬ ያለ ነው ትዝ ሊለን የሚገባ የክርስቶስ መስቀል መሆን እንደ አለበት ነው ። ትዝ ማለትም ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል ።

እግዚአብሔር በአማናዊ ቃሉ የተናገረውና ነቢያትም በትንቢት ጕዞአቸው ዓለምን ከአዳረሷት በኋላ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ዕውነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ለብሶ ሰው ሆኖ በዓለም ላይ እየተመላለሰ ያስተምር ጀመር ትምህርቱንም የጀመረው ማቴዎስ ወንጌላዊ የጻፈውን በም ፳ ፡ ቁ ፡ ፳ ላይ ብንመለከት በቂ መረጃ ሊሆነን ይችላል ። ከ፳—፳፩ ተመልከት ።

ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ ላይ ጽፎልናል ሮሜ ፮ ቁ ፱—፬ ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው አስቀድመው በትንቢት ባስተማሩ ጊዜ የመከራን ጽዋ የተቀበሉት በዘመኑ ለነበሩትም ሆኑ ዛሬ ስላለነው ታላቅ አብነት ሊሆነን ስለሚችል ሁል ጊዜ ሊታወሰን የሚገባ የክርስቶስ መስቀል መሆን እንዳለበት ነው ማስታወስም ብቻ ሳይሆን የመከራን ጽዋዕ መቅመስ ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆን አለበት ።

ነቢያት ያድነናል ብለው ገና በትንቢት ደማቸውን እንዳፈሰሱ ሁሉ እኛስ በክርስቶስ ደም ድነናል ብለን ደማችንን እስከ ማፍሰስ ድረስ ክርስቶስ በደሙ ለዋጃት ቤተ ክርስቲያን ብንመሰክር ምን የሚአግደን ነገር አለ ?

ርሱም ራሱ እኔን የሚወድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ ነፍሱንም ሊአድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚአጠፋ ሁሉ ያገኛታል ብሎ መመሪያውን በአምላካዊ ቃሉ ነግሮናልና በዚህም መሠረት መስቀሉን ተሸክመው መንገዳቸውን ወደ ክርስቶስ ያቀኑ እውነተኞች ክርስቲያኖች ከሐዋርያት ጀምረው እስከ አለንበት ዘመን ድረስ መጠናቸውን መወሰን ስለማንችል በአምላካዊ ዕውቀቱ ለሚመረምር እግዚአብሔር ብንተወው ይሻላል ።

## ከአቅም በላይ መራመድ

ከላይ እንደ ገለጽሁት ሁሉ ሰው ስሑት ፍጥረት እንደመሆኑ መጠን የሰው ልጆች ሁሉ አምላክን ዓይን በዓይን ለማየት ሽተው ለልዩ ልዩ ቅርጻ ቅርጽ ሲሰግዱ በመገኘታቸው እግዚአብሔር በግዙፍ አካል ተገልጾ በመካከላቸው እየተመላለሰ ካስተማራቸውና ለሕይወታቸው የሚሆን ሥራ ከሠራላቸው በኋላ በሃይማኖት እንዲከተሉት ወንጌልን ተሸክመው በግብር እንዲመስሉት አዘዛቸው እግዚአብሔር ስለሰው ሕይወት የፈጸመው የቸርነት ሥራና አምላካዊ መግቦት መስፈሪያና መለኪያ የሌለው ሲሆን መተንተንና ማስረዳት አይቻልም ።

የሥራውንም ውጤት ያስገኘው መስቀል ነው ። ከላይ ወደታች ከግራ ወደቀኝ የተሠመረ ነገር ስናይ መስቀል ነው እንላለን በዚህ መልክ ሁሉ የክርስቶስን የሥራውን ፍሬ በሙሉ ማጥናት ይቻላል እንግዲህ ምልክት የሚፈልጉ ቢኖሩ ሊአውቁት የሚገባቸው የእግዚንብሔር ጥበብ ይህ መስቀል ነው ብርታት የሚያሳያቸው ቢኖሩ ሰነፎች እንደ ስንፍና ያመኑትና ፤ የዳኑትና የሚረዱበት የእግዚአብሔር ኃይል ይህ መስቀል ነው ።

ነጻነታቸውን የሚወዱ ቢኖሩ በቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ዘለዓለም የሚአበራላቸው የነፃነታቸው ምልክት ሰንደቅ አላማቸው ይህ መስቀል ነው ነገር ግን ለኢትዮጵያ ምእመናን የመስቀሉ ምሥጢር እንግዳ ባይሆንባቸውም በይበልጥ ሰፋ አድርገው ቢመለከቱት ኃይላቸውም ጉልበታቸውም መድኃኒታቸውም የእግዚአብሔር ስምና መስቀሉ መሆናቸውን ያምናሉ ።

ለተከታዩም ትውልድ ሳይቆጠቡ ያስተምራሉ ያስረዳሉ ዛሬም ወደፊትም እስከ ዓለም መሠጨረሻ ድረስ እንግዲህ የስቅለ





www.ethiopianorthodox.org

ቱን በዓል ስናከብረው የምንኖረው ከዚህ በላይ በተገለጸው ጽኑዕ መሠረት አድርገን ስለሆነ ከመስቀሉ ዓላማ መናወጽ የለብንም አይኖርብንምም ።

ለእርሱ ሕማም ሞት ለእኛ ግን ክብር ጌትነት ከሆነው ከክርቶስቶስ መከራና መስቀል በስተቀር ሌላ መመኪያ (መድኃኒት) ዓርማ የለንምና የስቅለትን በዓል በየዓመቱ ስናከብረው ዘለዓለማዊ ደስታ ሊሰማን ይገባል ።

የጀብዱ ሜዳያችን የድል አክሊላችን የ ክርስቶስ መከራና መስቀል ስለሆነ እስከ ዛሬ ድረስ ሀገራችን ኢትዮጵያ ተጠብቃ የምትኖረው ሐፁረ መስቀሉ እንደ መጋረጃ እንደ ጦር ዘበኛ ሆኖ እንደ ነበረ የም እመናን ልቡና ሁሉ የሚረሳው አይመስለንም ስለዚህ ነው ምእመናን በየዓመቱ

የስቅለትን በዓል በየሰበካቸው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ተሰብስበው ከጥዋት እስከ ዕርበተ ፀሐይ ድረስ በስግደትና በጸሎት የሚውሉት ።

በመጨረሻም የክርስቶስን መከራ (ግርፋት ለማስታወስ ያህል በወይራ ቅጠል ተጠብጥበው ንስሓቸውን ተቀብለው ወደ ቤታቸው የሚመለሱት ነው የወይራውም ቅጠል ሊታወንቱ እንደሚሉት የምሥራች መገለጫ ነው ማለት ከይብስተ ኃጢአት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የመመለሻችን ምልክት ነው ሲሉ በሰፊው ተንትነው ያስረዳሉ ።

ልዑል እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ መንግሥቱን እንዲአወርስን እየተመኘሁ እንኳን ለዚህ ዕለት አደረሳችሁ ።

አባ ብርሃኑ ካግ የስብከትና ማስታወቂያ መምሪያ ኃላፊ ።



# ተንሥአ ኢሀሎ ዝየሰ ግቱ ፳፰ ቍ/ ፩

ተንሥኢል ከዚህ (በመቃብር ውስጥ) የለም ይህ የምሥራች የተሰማው ክርስቶስ የሞትን ማሠሪያ ፈትቶ በተነሣበት ሌሊት ነው ጠላቶችን በተንኮል መቃብሩን በቁልፍ ቆልፈው ዘበኞች ቀጥረው ቢያስጠብቁም የክርስቶስ የክብር ዘቦች የኃይሉ መገለጫዎች መላእክት ደግሞ በመቃብሩ ዙሪያ እንደ አሸን ፈስሰው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ትዕግሥቱን ችሎታውን ሲያደንቁ አድረዋል በዚህችው ሌሊት ተአማኞች የሆኑ ቅዱሳት አንስት ሽቱቸውን ይዘው በድኑን ሊቀቡ ወደ መቃብሩ ሲሔዱ እንደአጋጣሚ ከተነሣ በኋላ ደረሱ በመቃብሩ ዙሪያ ከነበሩት መላእክት አንዱ፣ ተንሥኢል ከዚህ የለም አላቸው ለጊዜው ሲነግ ባያዩም ትልቅ የምሥራች ነበር ።

ክርስቶስ ተንሥኢል ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ድል አድርጎ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተንሥኢል ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ታፍኖ አልቀረም ገዳዮች ያሰቡት ገድለው በመቃብር አፍነው ለማስቀረት ነበር ይሆን የተንኮል ምኞታቸውን ለመፈጸም በመቃብር በቁልፍ ቆልፈው ለማስቀረት ነበር ይሆን የተንኮል ምኞታቸውን ለመፈጸም መቃብሩን ቆልፈው የሌሊት ዘበኞች የተባሉት ሊቈጣጠሩ መድበው ነበር ማቴዎስ ፳፯ቍ/፷፮ ይህ ሰይጣናዊ ምኞት ከሽፎ ዘበኞች የተባሉት ሊቈጣጠሩት ባልቻሉት ሁኔታ የክርስቶስ ትንሣኤ አበራ በዚህ ጊዜ ጠላቶች ተበተኑ የሚጠሉት ከፊቱ ሸሹ ትንሣኤውን ለማየት አልቻሉም በክርስቶስ ፊት ቀጥ ብለው ለመቆም አልቻሉም ተብረከረኩ የትንሣኤን ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ስንመለከት ክርስቶስ ከዕንቅልፉ እንደነቃ ኀልማሳ ቆፍጠን ብሎ በመቃብሩ ጠርዝ ላይ ቆሞ በመቃብሩ ዙሪያ ደግሞ እንዲጠብቁ የተመደቡት ኀረምሶች ፊታቸውን ወደ መሬት ደፍተው ተንከባለው ወድቀው እናያለን አወዳደቃቸው የዕንቅልፍ አልነበረም የፍርሃት የድንጋጤ የመሸነፍ ነው ዓለም ከስሕተቱ አይማርም አሁንም የትንሣኤን ኃይል ለማፈን እግዚአብሔርን ቀብር ማለት በቍጥጥሩ ውስጥአድርጎ ብቻውን ለመኖር ይፈልጋል ከንቱ ምኞት አያጥጣውም እግዚአብሔር አሸናፊ ነውና በዚህ ፈንታ የሰው ልጅ ፊቃዱን ለእግዚአብሔርገዳይ ቢጥል ራሱን ለእግሊአብሔር ቢያስገዛ፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለርሱ ነጻነት የተፈጸመ መሆኑን ይገነዘባል የትንሣኤን ብርሃን ለማየት ይበቃል ሕይወትንም ያገኛል የትንሣኤ ብርሃን ሕይወትነቱ በክርስቶስ ለሚያምኑ ነው ፤ ለማያምኑ ግን የሚያስደነግጥ ነው የብርሃኑ ፀዳል የሚያብረከርክ የሚያፍገመግም እንደ ደንጊያ እንደ ኳስ መሬት የሚያንከባልል ነው ፤ እንደነዚያ መቃብር ጠባቂዎች

ቤተ ክርስቲያን ባለ ዘመኗ ኹሉ የክርስቶስን የትንሣኤ ድል ላልሰሙ እያሰማች ላላወቁ እያሳወቀች ሐዋርያዊ ግዴታዋን ትፈጽማለች ። ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን የነገሠ ለሰው ልጆች ሕይወት ን የሚሰጥ ሕያው ዘለዓለማዊ ንጉሥ ነው እንጅ በመቃብር ተቆልፎበት የሚኖር ደካማ አለመሆኑን በአደባባይ ትሰብካለች ።

እኛም የክርስቶስን ትንሣኤ በየዓመቱ የምናከብረው ያለፈውን ድርጊት በታሪክ መልክ ለማስታወስ ብቻ አይደለም የተነሣው ክርስቶስ አሁን ዛሬ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ነግሦ መኖሩን በማመን የትንሣኤን ብርሃን በእምነት ለመቀበል ተዘጋጅተን ነው በእርግጥ የትንሣኤ በዓል በደረሰቍጥር



www.ethiopianorthodox.org

ድግሥ ይደገሣል ዘመድ ከዘመዱ ጋር ይጠያየቃል አብራ ቅዳ ይባላል ድርጊቱ አይገባም አንልም የደስታ ቀን የነጻነት ቀን ነውና ነገር ግን የትንሣኤን ዕለት የምናስታውሰው ሌላም ብዙ አለ በትንሣኤው ዋዜማ ክርስቶስ ነፍሶቻቸው ታሥረው ወደ ነበሩት ሰዎች እንደሔደና ነጻነትንም እንደሰበከላቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ይመሰክራል ።

የዛሬ ክርስቲያኖች እኛም የትንሣኤን በዓል ስናከብር ከመቃብር ባልተሻለ ኑሮ የሚኖሩትን በኃጢአት ዓለም የታሠሩትን በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዘውየሚማቅቁትን ወንድሞቻችንን እኅቶቻችንን ልናስታውሳቸውና ፤ ልናስባቸው ይገባል የትንሣኤን ቁርሳችንን ምሳችንን ከነሱ ጋር ብንመገብ የተነሣው ክርስቶስ ማዕዳችንን ይባርክልናል በትንሣኤው በረከት እንረካለን ።

ሞት የሕይወት ፍጻሜ አለመሆኑን ከክርስቶስ ትንሣኤ እንማራለን ቤተ ክርስቲያን ስለሰው ትንሣኤ ስለ ዓለም ፍጻሜ የምታስተምረውን ትምህርት የማያውቁ አንዳንድ ሰውች ሕይወታቸው በሞት የሚያልቅ ይመስላቸዋል እነዚህ ሰዎች የመንፈስ ጭንቀት የሚያሰቃያቸው ተስፋ የቆረጡ ናቸው ክርስቲያኖች ግን የራሳቸውን ትንሣኤ በክርስቶስ ትንሣኤ ያረጋገጡና የተማሩ ስለሆነ ምድራዊ ሕይወታቸው' ቢያልፍ ሰማያዊ ሕይወት እንደሚጠብቃቸው ያምናሉ ካልዕ ቆሮንቶስ ፩/፬ ክርስቶስ የተነሣው የኛን ትንሣኤ ሊያስተምረን ነውና ።
ክርስቶስ ተነሥቶአል በመቃብር ውስጥ የለም

እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ

አባ ጎርጎርዮስ

ጳጳስ ዘሸዋ ።



# ማ ዕ ዶ ት ፤

«ፋሲካ ብሂል ማዕዶት ብሂል»

እስኪያልፍም የሚያልፍ ነገር የለም ፤ ትናንት ለሰው ልጅ የመከራ ሌሊት የነበረው ዘመነ ፍዳ አልፎ ዓመተ ምሕረት ከተተካ ቆይቷል ፤ ይህም የሆነው የጥንተ ተፈጥሮና የሐዲስ ተፈጥሮ ሠራዒ መጋቢ እንዲሁም ትንሣኤና ሕይወት በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው ።

በክርስትና ዘመን አቆጣጠር ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለው አዲስ ዘመን ማለት ዘመነ ክርስትና እንደ ጊዜው ደግነት «ዓመተ ምሕረት» ተብሎ በጊዜው ሰው ሲሰየም በነቢዩ ኢሳይያስ ስያሜ ደግሞ «ዓመተ እግዚአብሔር» ተብሎ ይጠራል ። (ሉቃ ፬ ፤ ፲፯—፲፱) ።

በዚህም የእግዚአብሔር ዓመት እጅግ በጣም የተከበሩ የሃይማኖትና የሕዝብ በዓላት ነበሩ አሉ ፤ ከእነዚህም አንዱ ጥንትም አሁንም የዓመቱ ከፍተኛ በዓል የሆነው ማዕዶት ወይም ፋሲካ ነው ። ፋሲካ በዘመነ ብሉይ የድኅነት ሥጋ በዘመነ ሐዲስ ግን የድኅነት ሥጋና የድኅነት ነፍስ ክብረ በዓል በሌላም አነጋገር የነፃነት ቀን ስለ ሆነ እጅግ በጣም የተከበሩና በሃይማኖት ታሪክም የከፍተኛውን ምዕራፍ የያዘ በእርግጥ ዓቢይ በዓል ነው ። «ማዕዶት» የሚለውም ቃል የሚያረጋግጠው የዚህን ምስክርነት እውነተኛነት ነው ።

በመሠረቱ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ርእስ የተነሣው ስለ ፋሲካ በዓል ምንነት ለመተረክ ከሆነ ዘንድ በተጠረገ ጎዳና ወደ በዓሉ ታሪክ ለመግባት በቅድሚያ «ማዕዶት» ስለሚለው ቃል ትርጉም ማብራራት ያስፈልጋል ። «ማዕዶት» ማለት ፋሲካ፣ፋሲካ ማለትም ማዕዶት ማለትነው። ይህንም በበለጠ ግልጽ ለማድረግ ማዕዶት ማለት በአጭሩ «መሸጋገሪያ» ማለት ሲሆን ፋሲካ ማለትም ትርጉሙ ያው እንደ ማዕዶት መሸጋገሪያ ማለት ነው ። ልዩነቱ ማዕዶት የሚለው ቃል «አደወ ተሻገረ» ከሚለው ግዕዝ የወጣ ሲሆን ፋሲካ የሚለው ቃል ግን «ፓስአበር ፓስክ ፓስሰል ወይም «ፔሳህ ከሚለው የዕብራይስጥና እንዲሁም ሌላ የውጭ ልሳን የተወረሰ የተውሶ ቋንቋ መሆኑ ብቻ ነው ።

ማዕዶት ወይም ፋሲካ በዘመነ ብሉይ የብሉይ ኪዳን በዘመነ ሐዲስ ደግሞ የሐዲስ ኪዳን ጽድቅ የተፈጸመበት በዓል ስለሆነ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ ሰዎች ዘንድ የተከበረ የወል በዓል ነው ። የዘመነ ብሉይ ታሪክ እንደሚያስረዳው ለአብርሃም በተሰጠው ቃል ኪዳን ሥር የነበሩ አበውና ውሉድ ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ከተሸጋገሩበት ጊዜ ጀምሮ ለማንኛውም «ሕግ መጽሐፋዊ» ሁሉ መሠረትነት ያላቸው ልዩ ልዩ ሕግጋት ነበሯቸው ፤ ከእነዚህም አንደኛው ክፍል በዓላትን ማክበር ሲሆን በዚህ ሕግ መሠረት በየዓመቱ በከፍተኛ ስሜትና ደስታ ከሚከበሩት የዓመት በዓላትም አንደኛና ዋነኛው በዓለ ፋሲካ ወይም ማዕዶት ነበር ። ሌሎቹ በዓላት ግን ከፋሲካ በኋላ ፋሲካንና በፋሲካም ምክንያት የተገኙትን ተከታታይ ድሎች በደስታ ለማሰብ የሚከበሩ በዓላት ነበሩ ። ይህም ማለት እሥራኤላውያን የሚያከብሯቸው በዓላት ሁሉ በረድኤተ እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር የወጡበትንና ከዚያም ወደ ተስፋ ምድር የገቡበትን እንዲሁም ለአራት መቶ ዓመታት ያህል



www.ethiopianorthodox.org

ወደ ተለዩዋት ውድ ሀገራቸው ተመልሰው የምድራቸውን ፍሬ ለመቅመስ የበቁባቸውን ዕለታት ለማሰብ ከሆነ ዘንድ የዚህ ሁሉ ታሪክ መነሻው ፋሲካ ወይም ማዕዶት በመሆኑ ነው ። በሌላም አነጋገር ፋሲካ የዘመኑ ብሉይ በዓላት ሁሉ በዙር ሲሆን ሌሎች በዓላት ከፋሲካ በኋላ የተገኙ የፋሲካ በዓል ምክትሎች ማለት ውጤቶች ናቸው ። በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ከፋሲካ በኋላ ህልውና ያገኙትን ሌሎች የዘመኑ ብሉይ በዓላት ከዚህ ላይ በስም መጥቀስ ቢያስፈልግ የሚከተሉት ነበሩ ።

ሀ/ ዕለተ ሰንበት ፣ በየሳምንቱ የሚከበር የዕረፍትና የደስታ ቀን (ዘሌ ፣ ፳፫ ፣፫፣

ለ/ በዓለ ናዕት እሥራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ በችኰላ የወጡበትን ሌሊትና ከዚያም በኋላ በሰፈሩበት ምድር ምድረ በዳ ያልቦካ ሊጥ ቂጣ እየጋገሩ በመብላት ያሳለፉትን የችግር ሰዓት ለማሰብ በአይሁድ ዓመት አቈጣጠር በመጀመሪያው ወር ከበዓለ ፋሲካ ቀጥሎ ለሰባት ቀናት ያህል የሚከበር የቂጣ በዓል (ዘሌ ፣ ፳፫ ፣ ፮) ።

ሐ/ በዓለ ጰንጠቆስጤ ወይም በዓለ ሃምሳ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ወጥተው ለሀገራቸው የምድር ፍሬ ስለበቁ የመከርን ወራት በጸሎተ ቡራኬ የሚጀምሩበትና ከሰባት ሱባኤ በኋላም እንደገና ከምድራቸው ፍሬ መሥዋዕት በማቅረብ የተቀደሰ ጉባኤ የሚያደርጉበት በዓልና የመከር በዓል (ዘፀ ፳፫ ፣ ፲—፲፱) ።

መ/ በዓለ መጸለት እሥራኤላውያን ከመከር ክታች በኋላ ወደ ተስፋ ምድር ገብተው አርሰው አዝምረው የበረከትን ፍሬ ለመቅመስ በመብቃታቸው በየዓመቱ ስለ አዲሱ መከር ለእግዚአብሔር ምሲጋና የሚያቀርቡበትና እንዲሁም ከግብፅ ምድር በወጡ ጊዜ በቅጠል ዳስ ውስጥ የኖሩበትን የችግር ወቅት ለማሰብ በሰባተኛው ወር ከእሥራኤል አምስተኛው ቀን ጀምሮ ለሰባት ቀናት ያህል የሚከበር የዳስ በዓል (ዘዳ ፣ ፲፮ ፣ ፲፫ —፲፮ ፤ ዘሌ ፣ ፳፫ ፣ ፴፩—፵፩።

ረ/ ዕለተ አስተሥርዮ ሕዝቡ የኃጢአት መሥዋዕት በማቅረብ በጾምና በጸሎት ኃጢአታቸውን ወደ እግዚአብሔር የሚናዘዙበትና ሊቀ ካህናቱም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የሥርዩት መሥዋዕት የሚያቀርቡበት በአመት አንድ ጊዜ በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን የሚከበር ልዩ የንስሓ ቀን (ዘሌ ፳፫ ፣ ፳፫—፴፫) ።

ሰ/ የማደስ በዓል በአረማዊው አንጥያኮስ የፈረሰውንና በአረማውያን መሥዋዕተ ጣእት የጎደፈውን ቤተ መቅደስና መሠዊያ በይሁዳ መቃቢስ አማካይነት እንደገና የታደሰበትን ወቅት ለማስታወስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ውኃ በመርጨትና መብራት በማብራት ከዐመት አንድ ጊዜ በደመቀ ሁኔታ የሚከበር የደስታ በዓል (፩ ፣ መቃበ ፣ ፬ ፣ ፶፱ ፣ ፪ ፣ መቃብ ፣ ፲ ፣ ፮—፰ ፤ ዮሐ ፣ ፲ ፣ ፳፪ ።

ሸ/ የፋሪም በዓል ንግሥት አስቴር በወገኖቿ ላይ የተደረገውን ደባ በረቀቀ ጥበብ በማክሸፍና ለወገኖቿ በተቈፈረውም ጉድጓድ ራሱ ጠላት እንዲገባበት በማድረግ ያስገኘችውን ድል ለማሰብ በዐሥራ ሁለተኛው ወር በዐሥራ ዐራተኛውና በዐሥራ አምስተኛው ቀን በከፍተኛ ደስታ የሚከበር ዓመታዊ በዓል (መጽ አስቴር ፫ ፣ ፮ ፣ ፱ ፣ ፳—፴፪) ።

በአዋጅ የሚከበሩ የዘመኑ ብሉይ በዓላት ዋና ዋናዎቹ እነዚህ ሲሆኑ ሌሎችም እንደ በዓል መጥቀዕ ማለት የመለከት በዓል ያሉ ንዑሳን በዓላት ነበሩ ። ሁኖም አስቀድሞ እንደተገለጠው በዓለ ፋሲካን የሚልቅና የሚቀድም በዓል ባለመኖሩ በ



ዓሉ በዘሙኑ ብሉይ ምእመናን ከሌላው በተለየ አከባበር ሲከበር ኑሮዋል ። በመሠረቱ የእሥራኤል ሕዝብ በዓለ ፋሲካን የሚያከብረው ጥንታውያን አበው በግልፅ ምድር በስደት በነበሩበት ዘመን ከፈርአናውያን ይደርስባቸው ከነበረው የጭቆናና የባርነት አገዛዝ ነፃ የወጡበትንና እንዲሁም የገዥዎቻቸውን ዐመፅ ለመግታት ከወረዳውና እነሱንም ነፃ ካወጣው ከአሥረኛው መቅሠፍት ከገዥዎቻቸው ተለይተው የዳኑበትን የድኅነትና የነፃነት ቀን ለማሰብ ነበር ፣ በዓሉም የሚከበረው የአይሁድን የኒሳን ወር (ሚያዝያ) በገባ በአሥራ አራተኛው ቀን ሲሆን የበዓሉ ቀዳማዊና ደኃራዊ አከባበር ሥርዓትም በአጭሩ እንደሚከተለው ነበር ።

በመሠረቱ የፋሲካ በዓል ታሪክ የሚጀምረው እሥራኤላውያን ከምድረ ግብፅ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ነው ። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፲፱፻፶ ዓመተ ዓለም ከከነዓን ሕዝብ ላይ የረሀብ እልቂት ስለ ደረሰ ይህ ዘመኑ ዓፀባ ለሕዝቡ ዘመነ ስደትም ሁኖ ነበር ። በዚያን ጊዜ ያዕቆብ አሥራ ሁለቱን ነገድ ይዞ ወደ ግብፅ በመፍለስ የመጀመሪያው ስደተኛ ለመሆን ሲገደድ ከዚያ በኋላ ደግሞ ዘሮቹ ሁሉ በግብፅ ምድር መፃተኛ በመሆን ለአራት መቶ ዓመታት ያህል ቆይተዋል ።

ዘፀ ፲፪ ፣ ፴ ። ዘፀ ፣ ፴፮ ፣ ፩—፯) ፣ ሁኖም በዚህ ጊዜ የግብፅ ገዦች እያንዳንዱን እሥራኤላዊ የሚሸጥ የሚለውጥ የግል ባሪያ አድርገው ከመግዛታቸውም በላይ «አገሬን» የሚል ወንድ እንዳይወለድ የወሊድ ቁጥጥር እስከ ማድረግ ደርሰው የግፍዕንና ጭቆና አገዛዝ ስለአጸኑባቸው (ዘፀ ፣ ፪ ፣ ፳፫ — ፳፭ ፣ ፫ ፣ ፯—፲) ግፉ በእግዚአብሔር ዘንድ ታይቶ የማይታለፍ ኃጢአት ሆነና የእሥራኤል አምላክ እነዚያን ሕዝቦች ከዚያ ጭቆና ነፃ ማውጣትን የጊዜው ዓቢይ ተግባር በማድረግ በፈርኦንና በፈርዖናውያን ላይ ዘመተ ፣ የግብጻውያን ገዦች አሊቃ የነበረው ፈርኦን እነዚያን ጭቁን ሕዝቦች ነፃ እንዲለቀቅ የተለያየ ምክርና ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም በእምቢተኛነትቱ ስለ ጸና በዐሥር ዓይነት መቅሠፍት አሥር ጊዜ ተደብድቧል ።

አሥረኛው መቅሠፍት ግን የማያዳግም በትር ስለነበር ለእሥራኤላውያን ነፃ መውጣትና ለበዓለ ፋሲካም መፈጠር ዋና ምክንያት ሁኗል ። (ዘፀ ፣ ፲፩ ፣ ፲—፲ ። ፲፪አ ። ፩—፴፬) ። ግፈኞቹ አሕዛብ በመጻፋቸው ሥር ያስገቧቸውን ጭቁኖች እንዲለቁ በአሥረኛው መቅሠፍት በተመቱበት ወቅት እሥራኤላውያን አብረው እንዳይጎዱ እያንዳንዱ ባለቤት የፋሲካን በግ አርዶ በደሙ የቤቱን መቃን መድረክ እንዲረጭ አምላካዊ ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበር ። ትእዛዙ በትክክል ስለተፈጸመም የታዘዘው መቅሠፍት ተልእኮውን የፈጸመው በእያንዳንዱ ቤት ለቅሶና ዋይታ እስኪሆን ድረስ ቀይ ምልክት ያለበትን የእሥራኤላውያን ቤት እያለፈ የግፈኞችን ቤት በመምታት ነበር ።

እነዚህ አመታት ጭቁን እሥራኤላውያንን ነጻያወጣ የድል በትር ሲሆን ለነበረውና ላለው የፋሲካ ክብረ በዓል መነሻ የሆነውም በዚያን ጊዜ ለአምልኮት የተሠዋውና የፈሰሰው ደም ነበር ። ፋሲካ ወይም ማዕዶት ማለት ማለፍ መሻገር ማለት እንደ መሆኑ መጠን በዚያ ሰዓት ያመቅሠፍት ይህን ቀይ ምልክት እያየ በማለፍ ምክንያት ማለት እንደ መሆኑ መጠን በዚያ ሰዓት ያመቅሠፍት ይህን ቀይ ምልክት እያየ በማለፍ ምክንያት ያንጊዜ በዚህ መንገድ የቀረበው መሥዋዕት «የእግዚአብሔር የማለፉ መሥዋዕት»ተብሎይጠራል(ዘፀ፣ ፲፪፣፳፳፯) ያን ጊዜ በዚህ መልክ የተጀመረው



www.ethiopianorthodox.org

በዓለ ፋሲካ በዘመነ ሐዲስም እንደገና በሌላ መልክ ስለታደሰ የዘለዓለም ሥርዓት ሁኖ ይከበራል ። እሥራኤላውያን ወደ ተስፋ ምድር ከገቡ በኋላ በዓለ ፋሲካን የሚያከብሩት የሩቁም የቅርቡም በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም በመሰብሰብ ሲሆን ከዚያም ዋናው ቦታ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ነበር ። በዚህ ቦታ በሚደረገው የበዓል አከባበር ካህናቱ በቤተ መቅደሱ ዓውደ ምሕረት በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የታረደውን የፋሲካ በግ ደም ይዘው ከዓውደ ምሕረቱ እስከ ቤተ መቅደሱ ድረስ በሁለት ረድፍ ማለት የወርቅ ጽዋዕ የያዙት በአንድ ረድፍ የብር ጽዋዕ የያዙት ደግሞ በሌላ ረድፍ ከተሰለፉ በኋላ የያዙትን ጽዋዕ እየተቀባበሉ በማሳለፍ የመጨረሻው ካህን በሥርዓተ ጸሎት መንበሩን እንዲረጭ ይደረግ እንደ ነበርና ይህንም የሚያደርጉት ከመዝሙር ፻፲ እስከ ፻፳ ያለውን የምስጋና መዝሙር በመዘመር እንደነበር ታልሙድ የተባለው የአይሁድ መጽሐፍ ይተርካል ። ይህ በዓል ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ድረስ ለ፩ሺ፫፻፶ ዓመታት ያህል በዚህ ዓይነት ሲከበር ከቆየ በኋላ በክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን ደም ፋሲካው በፋሲካ በዓሉ በበዓል እንደገና ስለታደሰ የፋ የፋሲካ በዓል አሁን ያለውን መልክናቅርጽ ሊይዝ ችሏል ።

በፋሲካም ሆነ በሌሎች የዘመነ ብሉይ በዓላት ይቀርብ የነበረው የሰላምና የድኅነት መሥዋዕት ወደፊት በተስፋ ይጠበቅ ለነበረው አማናዊ መሥዋዕት መንገድ ጠራጊ በመሆን ያገለገለ ትንቢትና ምሳሌ እንጂ ራሱ አማናዊ የድኅነት ዓለም መሥዋዕት አልነበረም ፣ በአጭሩ ለመናገር የድኅነተ እሥራኤል እንጂ የድኅነተ ዓለም የድኅነተ ሥጋ እንጂ የድኅነተ ነፍስ ዘለማዊ መሥዋዕት አልነበረም ። በእርግጥ በዘመነ ብሉይም ቢሆን ደም ያለ ደም ስለማይነፃ ደም ሳይፈስ ሥርየት (ይቅርታ) አልነበረም ። ሁኖም ይህ መሥዋዕትና ሥርዓት ለዘለዓለማዊው መሥዋዕትና ድኅነት ምሳሌ እንደ መሆኑ መጠን እሥራኤላውያን ራሳቸውን በረድኤተ እግዚአብሔር ለማስጠበቅ አማናዊ መሥዋዕት በሆነው በሐዲስ ኪዳን ደም አምሳል የብሉይ ኪዳን ደም በማፍሰስ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ ይቅር ባይ የሆነው አምላክም በክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን ደም ለሚገኘው ዘለዓለማዊ ድኅነት ምልክት የሆነውን የኃጢአት ሥርየት በማድረግ ሕዝቡን በረድኤቱ ይጠብቃቸው ስለነበር የብሉይ ኪዳን ደም ዋጋቢስ አልነበረም ። አሁን ግን ፀሐይ እስኪወጣ ከዋክብት እንደሚያብለጨል በክርስቶስ መሥዋዕትነት የብሉይ ኪዳን ደም በሐዲስ ኪዳን ደም ስለተተካ በአሁኑ ጊዜ በዓለ ፋሲካን የምናከብረው በብሉይ ሳይሆን በሐዲስ የኪዳን ደም ፋሲካነት ነው ።

የሐዲስ ኪዳን ደም ባለቤት የሆነው ክርስቶስ የመሢህነት ሥራውን በግልጽ ጀምሮ የንስሓና የሰላም ወንጌልን ለዓለም በማስተማር ሁለት ሦስት ፋሲካዎችን ካሳለፈ በኋላ የብሉይ ኪዳንን ደም በሐዲስ ኪዳን ደም ማለት ስለሰዎች ድኅነት ይፈስ የነበረውን የእንስሳ ደም በራሱ ደም በመተካት በፋሲካ ላይ ፋሲካ የሚያደርግበት ትክክለኛ ሰዓት ደረሰ ፣ ያን ጊዜ ዕለቱ ሐሙስ ቦታው ኢየሩሳሌም ጊዜው የብሉይ ኪዳን ፋሲካ በዓል ዋዜማ ሲሆን ፣ የበዓለ ፋሲካው አዘጋጆችም ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ፣ የፋሲካው በግ ታርዶ በቀድሞው ልማድ በተዘጋጀው የራት ግብዣ መጨረሻ ላይ ክርስቶስ ከፊቱ የቀረበው ኅብስትና ጽዋዕ አንሥቶ ባርኮ ቀድሶ «እነሆ ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው ፣ ይህም ጽዋዕ ለብዙዎች ኃጢአት ማስተሥረያ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው ። ብሉ ፣



ጠጡ» በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ማቴ ፳፮ ፣ ፲፯—፳፱) ። ክርስቶስ ይህን ያለውና ይህንም ያደረገው ስለሰው ልጆች ፀዋትወ መከራን ለመቀበልና ክቡር ደሙንም ለብዙኃን ቤዛ በማፍሰስ ድኅነተ ዓለምን ለመፈጸም በተዘ ፫በት ሰዓት ሲሆን ይህ ሥርዓት ከዚያ በፊት ያልነበረና ያልታወቀ በእርግጥ ፍጹም ሐዲስ ነበር ። ስለዚህ በዚያን ሰዓት የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት በሐዲስ ኪዳን ተተካ ፣ የብሉይ ኪዳንሥርዓት አክትሞ የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ተጀመረ በፋሲካ ላይ ፋሲካ ማለት በማዕዶት ላይ ማዕዶት ሆነ ስለድኅነተ ዓለም የተነገረው ትንቢትና የተመሰለው ምሳሌ ሁሉ በትክክል ተፈጸመ ፣ በዘመነ ብሉይ አይሁድ ይህን በዓል «ፋሲካ» ያሉት ከግብፅ የወጡበትንና ከባርነት ወደ ነፃነት የተሸጋገሩበትን እንዲሁም ከአሥረኛው መቅሰፍት የዳኑበትንና ባሕረ ኤርትራን በሰላም ተሻግረው ወደ ተስፋ ምድር የገቡበትን የድኅነትና የነፃነት ቀን ለማሰብ ሲሆን በክርስቶስ ክርስቲያን ለሆን ለእኛም ይህ ዕለት ከሞት ወደ ሕይወት ፣ ከኀሣር ወደ ክብር የተሸጋገርንበት ፣ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ የወጣንበትና ባሕረ ኃጢአትን በክርስትና እምነት በሰላም ተሻግረን ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለመግባት የቻልንበት የመሸጋገሪያ ዕለት ስለሆነ በእርግጥ ለኢያንዳንዳችን ፋሲካችን ሆኖአል ።

ይህ አነጋገር አዲስ ድርሰት አይደለም ፣ በዕልፍ አዕላፍ ነቢያትና ሐዋርያት ጻድቃንና ሰማዕታት ቃል የተመሰከረና በግብርም የተረጋገጠ ዘለዓለማዊ እውነት ነው። በምስክርነቱ እውነተኛነትና በሕይወቱ አዲስነት የዓለም እንግዳ ሰው የነበረው ዮሐንስ መጥምቅ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ (ዮሐ ፩ ፣ ፳፱)» በማለት የክርስቶስን ማንነት ራሱ አስቀድሞ በትክክል አውቆ ለዓለም ሲያስተዋውቅ ከዕለተ ዓርብ በኋላም ይህን የምስክርነት ቃል ያረጋገጠ ዮሐንሳውያን ብዙዎች ናቸው ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በራዕዩ «ለወደደን ከኃጢአትም በደሉ ላጠበን ለእሱ ክብርና ኃይል ይሁን (ራዕ ፣ ፩ ፣ ፮)» ሲል በሌላው መልእክቱ ደግሞ የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ያነፃናል (፩ ፣ ዮሐ ፣ ፩ ፣ ፯)» በማለት ስለ ክርስቶስ ደም ውጤት ይመሰክራል ። ዮዕብራውያን መልእክት የብሉይ ኪዳንን ደም ከሐዲስ ኪዳን ደም ጋር በማነጻጸር «የእንስሳ መሥዋዕት ሥጋን በማንፃት የሚቀድስ ከሆነ የክርስቶስ ደምማ ከሞተ ሥራ ኅሊናችሁን እንዴት ያነፃ ይሆን ? (ዕብ ፱ ፣ ፲፫—፲፭») በማለት አስደናቂ የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በበኩሉ» በመንፈስ ለመቀደስ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጪ ዘንድ ለተመረጡ ፀጋና ሰላም ይሁን (፩ ፣ ጴጥ ፣ ፩ ፣ ፮)» በማለት በክርስቶስ ደም ስለሚገኘው ፀጋና ሰላም ይናገራል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በቆላስይስ መልእክቱ» ክርስቶስ በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ) ቆላስ ፩ ፣ ፳)» በማለት በክርስቶስ ደም ስለ ተገኘው ሰላም ሲመሰክር በቆሮንቶስ መልእክቱ ደግሞ እሥራኤል ከግብፅ ሲውጡ የግብፅን እርሾ ከዚያው ግብፅ ትተው ወጥተው ያልቦካ ቡሆ እየጋገሩ መብላታቸውንና በአዲስ ቡሆ አዲስ ኑሮ መጀመራቸውን በአዲሱ ፋሲካ ከተጀመረው አዲስ ሕይወት ጋር በማነጻጸር እንግዲህ ያለ እርሾ የሆነውን አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ ፋሲካችን ክርስቶስ ተሠውቷልና ፣ ስለዚህ በቅንነትና በእውነት ቂጣ እንጂ በአሮጌ እርሾ ማለት በክፋትና በግፍ አይደለም ፣ ፩ ቆሮ ፭ ፣ ፯)» ሲል ስለ ክርስቶስ ፋሲካነትና ክርስቶስ ፋሲካቸው የሆነ ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

ከፋሲካ በኋላ ሊኖራቸው ስለ ሚገባው አዲስ ሕይወት ይገልጻል ።

በሐዲስ ተፈጥሮ የተገኘው ሐዲስ ሕይወት በክርስቶስ ደም የተዋጀ የደም ዋጋ መሆኑን ለማረጋገጥ የተጠሰጠው የቃል ምስክርነት ከብዙው በጥቂቱ ይህ ሲሆን ሌላው ዋና መረጃ ደግሞ የእውነተኞች አማንያን ሕይወት ነው ። እውነተኞች የክርስቶስ ተከታዮች በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ እምነት ተስፋና ፍቅር ስላላቸው በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው የሲኦልና የገሃነም ኑሮ አይናፍቃቸውም ፤ ክርስቶስ የሙታን በኩር መሆኑን ስለሚያምኑና እንዲሁም ትንሣኤ ሙታንንና የሚመጣውንም ሕይወት ተስፋ ስለሚያደርጉ በእነሱ ዘንድ የሥጋ ሞት የመጨረሻ ሕልፈት አይደለም ። ለቅድስናና ለሰማዕትነት አቅመ ቢሶች አይደሉም ፤ ሌላውን እንደ ራሴ መውደድና ለራሳቸው ሊደረግላቸው የሚፈልጉትን ሁሉ ለሌላው ማድረግ እንዲሁም በራሳቸው ላይ ሊደረግ የማይፈልጉትን በሌላው ላይ አለማድረግ ጠባብ በራቸው አይሆንም ፤ በክርስቶስ ደም አሮጌውን ሰውነት በአዲስ ተክተዋልና ፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ተገዥ ነው (ዮሐ ፰ ፡ ፴፬) ሲል ክርስቶስ እንደ ተናገረው ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ደም ከኃጢአት ባርነት ወደ ነፃነት ፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋግረዋልና እነሱ በዓለም ላይ ይሰለጥኑበታል እንጂ ዓለም በእነሱ ላይ አይሰለጥንባቸውም ።

የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለሁላችንም ፋሲካችን ነው ፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋግረንበታል ፤ አሮጌውን ሰውነት ከአዲስ ተክተንበታል ፤ ትንሣኤያችንን በትንሣኤው አረጋግጠንበታል ። ስለ ዚህ በዓለ ፋሲካውን በአዲስ እርሾ ማለት በአዲስ ሕይወት የሚያከብሩ እነሱ አዲስ ሰዎች ናቸው ፤ ለኃጢአት ሙታን ለጽድቅ ሥራ ግን ሕያዋን ይሆናሉ ፤ በደስታ ይጾማሉ ፤ ይጸልያሉ ፤ በደስታ ይፈስካሉ ። አምላክ ሆይ ትንሣኤህን ለምናምን ለእኛ ብርሀንህን ላክልን ።

መልካም ፋሲካ ለሁላችን
መልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን



የግል ቤተ መጻሕፍት

# በዓለ ሃምሳ ፤ (ርደተ መንፈስ ቅዱስ)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ከዕርገቱ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አባቴ የሚሰጣችሁን ተስፋ እስከምልክላችሁና ከላይ ኃይል እስከምትለብሱ ድረስ ከኢየሩሳሌም ከተማ አትውጡ በማለት ከቦታ ወደ ቦታ እንዳ ይዘዋወሩ ከሀገር ወደ ሀገር እንዳይሄዱ ለጊዜው በአንድ ቦታ ብቻ ተወስነው እንዲቆዩና የታዘዘላቸውን ተስፋ እንዲጠባበቁ አዘዛቸው ።

እነሱም ከአምላካቸው በተሰጣቸው መመሪያ ጸንተው ከትእዛዛቱ አንዳቸውንም ሳያጓድሉ በነቂሐ ሕሊና በሰቂለ ልቡና ሆነው ከላይ የሚላከላቸውን ተስፋ ምጽአተ መንፈስ ቅዱስን እየተጠባበቁ ተቀመጡ ። ዮሐንስ በኋላ ግን ማርቆስ በተባለው ደቀ መዝሙር እናት በማርያም ቤት ተሰብስበው በር መልሰው ቤት ዘግተው በአንድ ልብ ሆነው ሲጸልዩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነሣ በሃምሳኛው በዐረገ በዐሥረኛው ቀን ይጠባበቁት የነበረውን ተስፋ መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው ።

መንፈስ ቅዱስንም ሲልካቸው ላንቃ ላንቃባለው የእሳት አምሳል ወርዶ በየአንዳንዳቸው ላይ እንዲቀመጥ አድርጓል ። «ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በየአንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር» የሐሥራ ም ፤ ፪ ፡ ቁ ፡ ፪ ። ሐዋርያትም በዚህ ዓይነት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ያፍሩ ይፈሩ የነበሩ የማያፍሩና የማይፈሩ ድንጉፃን የነበሩ የማይደነግጡ የዚህን ዓለም መከራ የማይሰቀቁ ጊዜያዊ ተድላና ደስታ ድል የማይነሳቸውና የማያጠቃቸው የክርስቶስን ቃል ለመመስከር የበቁና የነቁ ፍጹማን ሆኑ በተጨማሪም በአንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ በ፸፪ ቋንቋ ለመናገር በቁ በዚያን ጊዜ ሕዝቡ እያንዳንዱ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ስለሰሙ እሊህ የገሊላ ሰዎች በራሳቸው ቋንቋ ለመናገር የማይችሉ እንዴት በየሀገራችን ቋንቋ ሊናገሩ ቻሉ እያሉ ይደነቁ ነበር የጌታችንን ሞትና ትንሣኤ ያላመኑ አይሁድ ግን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋና ኃይል ለማስተባበልና ለማቃለል ሲሉ ፈልቶ ያልወጣለት ጉሽ ጠጅ ጠጥተው ነው እንጂ እነዚህማ የምናውቃቸው የገሊላ ሰዎች አይደሉምን ? እያሉ ይዘባበቱባቸውና ያፌዙባቸው ነበር ።

በዚያን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስም በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ተነሳሥቶእናንት በኢየሩሳሌም የምትኖሩ የአይሁድ ወገኖች ሁሉ በነቢዩ በኢዩኤል «ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ» የሚለውን አታስተውሉምን በማለት በመጠጥ ኃይል ተገፋፍተው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አጋዠነት መሆኑን በትክክል ስለአስረዳቸው በትምህርቱ ፫ሺ ሕዝብ በአንድ ጊዜ ለማሳመን ችሏል ።

ይኸችም የማርቆስ እናት ቤት ወይም ጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ የወረደባት በመጀመሪያ ሐዋርያት በክርስቶስ ሞት ተደናግጠው አዝነውና ተክዘው አይሁድንም ፈርተው በውስጧ ተሰብስበው እንደ ተቀመጡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዝግ ቤት ገብቶ



www.ethiopianorthodox.org

ሰላም ለእናንተ ይሁን በማለት ከሙታን ተለይቶ መነሣቱንና ምሥጢረ ትንሣኤውን ያበሠረባት ሁለተኛም ሐዋርያት የመንፈፈስ ቅዱስን ልጅነት አግኝተውና ተቀብለው ምሥጢራትን የተናገሩባት ሌሎችም ታአምራታዊ ሥራዎች የተፈጸሙባት ታሪካዊ ቦታ ናት ።

እንግዲህ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ በጠቅላላ ዓለምን በዕፃ ተከፋፍለው እየዞሩ ለማስተማር ወስነው በአጭር ታጥቀው ተነሡ ለሥራም ተሰለፉ እንጂ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንብሮተ ዕድ ሹሞናል ብለው ሹመታቸውን የሥራ ፍጻሜ አድርገው ከማስተማር ወደኋላ አላሉም ።

የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያም በመሆናቸው ጽሙዳን በገድል ማለት በሥራቸው ጥምድ እንደ በሬ ቅኑት እንደ ገበሬ ሆነው ዓለምን ከስሕተት ጎዳና መልሰዋል ከአስገኛውና ከፈጠረው ፈጣሪ ጋርም አስተዋውቀዋል ። በዚህም ሥራቸው «የዓለም ብርሃን እናንተናችሁ» የሚል ስያሜ ከፈጣሪያቸው ተሰጥቷቸዋል እንግዲህ የሐዋርያትን ፈለግ ተከትለናል የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን አምነናል መንፈስ ቅዱስንም ተቀብለናል የምንል ሁሉ ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ሥራ አፈንግጠን መውጣት የለብንም ። መሪጌታ ከየን ወ/ማርያም



# ተአምራዊው ጠበል በጐጃም

በጎጃም ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት በባሕር ዳር አውራጃ በሜጫ ወረዳ በኢቻሌ ቅ/ጊዮርጊስ ቀበሌ ክልል የሚገኘው የአቡነ ዘርዓ ቡሩክን ጠበል መጋቢት ፳፫ ቀን ፻፹፫ ዓ/ም በአውራጃው የቤ/ክህነት ሥራ አሥኪያጅ በመ/ ጌታ ተሰማ ገብረ መስቀልና በዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጠኞች ቡድን ተጎብኝቶአል ።

ጎብኞቹ መጋቢት ፳፬ ቀን ፻፹፫ ዓ/ም ከባሕር ዳር ወደ መርዓዊ ጉዞ ካደረጉ በኋላ በመርዓዊ አዳር ሆና ከጠዋቱ ፩ሰዓት ወደ ጠበሉ በእግር ጉዞ በማድረግ ከዐርባ አምስት ደቂቃ ነሶሳወ እግር (የእግር ጉዞ) በኋላ በስፍራው ደርሰዋል በዚሁ ወቅት በጠበሉ የነበረው ተጠማቂ ሕዝብ ያንድ አነስተኛ ከተማ ሕዝብ ያህል ነበር በሕዝቡ መካከል አልፈን ወደ ጸሎቱ ሥፍራ ደረስን በጸሎቱ ሥፍራም ከአንድ ሺህ ያላነሰ የጠበልተኛው ጠበል መያዣ ዕቃ ዎች በቅደም ተከተል ተኮልኩለው ይታዩ ነበር ። ከተኮለኮሉት ዕቃዎች በላይ አትሮንስ ተዘርግቷል በአትሮንሱ ላይ የአቡነ ዘርዓ ቡሩክ ድርሳን ፤ የቅዱስ ጊዮርጊስ ገድል ፤ የሌሎቹም ተአምራትና ድርሳናት ሲነበቡ እስከ አምስት ሰዓት ድረስ ቆየ ከአምስት ሰዓት በኋላ አባ አድኅ ወይም አባ ወልደ ትንሣኤ የተባሉት መነኩሴ ጠበሉን አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ የሚለውን የቤ/ክርስቲያናችን ሥርዓተ ጸሎት አደረሱ ተጠማቂው ሕዝብ በቅደም ተከተል ተኮልኩሎ ተራውን ሲጠብቅ የተመለከትነው እስከ ሁለት ሺህ የሚገመት ነበር ፤ ይህም ሕዝብ በልዩ ልዩ አጋንንት ማለት የሰው ልጆች ጠላት የሆነው ሰይጣን አካላታቸውን በማቁሰል በማጎሳቆል በማሳበድና እጅግ ፀጣም አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ በማሰቀቅ ከሰብአዊ አቋም ውጭ አድርጎ ያሰቃያቸው ምስኪናን በሽተኞችን ተመለከተን ።

ከዚህም ሌላ ከአንድ ወረዳ አስተዳደር ያላነሰ የከተማ መንደር ክምችት አየን ይኸም ደግሞ ምንድር ነው? ብለን አንዳንድ ሰዎች ጠየቅን ፤ ለጥያቄው የተሰጠን መልስ ይህ መንደር የበሽተኞች መኖሪያ ወይም የመቆያ ቤት ነው የሚል ነበር ።

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው አባ አድኅ ወይም አባ ወልደ ትንሣኤን ለብቻቸው አግለን መጠይቅ አድርገንላቸዋል ። መጠይቁም ሥራቸው ምን እንደሆነ እንዲገልጹልን ነበር ፤ አባ አድኅ በኢቻሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለ፳ መታት ያህል በዲቁናና በቅስና እንዳገለገሉ አረጋግጠውልናል ። በዚሁ ቀበሌ የትዳር ወግ የሐዘንና የደስታ ሁኔታዎች እንደተፈራረቁባቸውም አውግተውናል ፤ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ከተክሊል ጋብቻ እስከ ቅስና ከዚያም አልፎ እስከ መዓርገ ምንኩስና ደረጃ እንደደረሱም አወያይተውናል ።

አባ አድኅ ባሳለፉት መልካም ዘመን ከሚወዱአቸው ሚስታቸው ጋር የሰላምና የደስታ ዘመን እንዴት እንዳሳለፉት ገልጸውልናል ። ይሁን እንጂ የሰው ሕይወት በምድር ላይ ያለው የኑሮ ገደብ ከየት እስከ የት እንደሆነ ከእያንዳንዱ ግለሰብ የተሰወረ ስላይደለ እያንዳንዳችን እንድንገነዘበው አሳስበው ያ የደመቀና የሞቀ ንብረታቸው መፍረሱንም አውግተውናል እርሳቸውም ከመንደሩ ወጥተው በሕገ ምንኩስና ተጠምደው በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ይኖራሉ ከጊዜ በኋላ ግን አባ አድኅ ጉልበታቸው እየደነዘዘ ዓይናቸው እየፈዘዘ ስለሄደ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ዘጌ ሊሄዱ ቁርጥ ሀሳብ አድርገው እንደነበር ገልጸዋል ፤ በዚህም



www.ethiopianorthodox.org

ሀሳባቸውን ለመፈጸም ወስነው ሳለ በሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጾ አባ አድኅ ስማ ወዴት ለመሄድ ነው የምታስበው? ብሎ ቢጠይቀኝ እንግዲህ እኔ አርጅቻለሁ ወደተወለድሁበት ወደዘጌ ገዳም ሄጄ ለመቀመጥ አስቤአለሁ አልሁት ፤ እርሱም መልሶ አትሄድም በዚህ ቦታ እንድ ታጠምቅ አዝዤ ሃለሁ ብሎኝ ተሠወረ ብለዋል ።

እኔም ነገሩ ለጊዜው ደነቀኝና እንደገና ችላ ብዬ ወደተወለድሁበት ቀበሌ ወደ ዘጌ ለመሄድ ተነሣሣሁ ፤ በነገራችን ላይ ዘጌ የሚባል ሥፍራ የሚገኘው በጣና ባሕር ውስጥ ነው አባ አድኅ ንግግራቸውን በመቀጠል አሁንም ልብሱና ፊቱ እንደፀሐይ የሚያበራ ሰው ታኅሣሥ ፲፩ ለ፲፪ ቀን ፹፪ ዓ/ም አጥቢያ ከፊቴ ቆሞ ስማ አለኝ አቤት ብዬ ደንግጬ ተነሣሁ ፊቱ ግን ላስተውለው ማለት በልክ ላየው አልቻልሁም ምን ብዬህ ነበር? ይህን የምታስበውን ሀሳብ ተወው በዚሁ አጥምቅ ብየህ አልነበረምን? አለኝ ከየት ሁኜ ነው የማጠምቀው ብዬ ጠየቅሁት ከጊዮርጊስ ጠበል አለፍ ብሎ አንድ በክረምት ጎርፍ የተቦረቦረ ሥፍራ አለ ፤ በዚያ ጠበል ይፈልቃል የዚህ ጠበል አጥማቂ ሁነህ ሕዝቡ ከደዌው እንዲፈወስ አዝዝሃለሁ ካለኝ በኋላ ለመሆኑ ዛሬ ዘመኑ ምንድር ነው? አለኝ እኔም ዘመነ ዮሐንስ ነው ዓመተ ምሕረቱም ፹፪ ወሩም ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ነው አልሁት ልክነህ ስለዚህ አጥምቅ የምልህም እኔ ዮሐንስ ነኝና ነገ ጠዋት ሄደህ ሥርዓተ ጸሎት በዚያ እንድታደርስ ብሎኝ ተሠወረ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፹፪ ዓ ም ሕዝቡን ሰብስቤ እኔ አንድ በብርሃን የተከበበ ሌሊት እየመጣ እንዳትሄድ በዚሁ ማጥመቅ አለብህ አለኝ ብዬ ያየሁትንና የሰማሁትንም ነገርኳቸው እነርሱም በእርግጥ አሁንም ቢሆን መሔድ የለብዎትም እንደታዘዙት ሥርዓተ ጸሎቱን እያደረሱ በተባለው ሥፍራ ሆነው ያጥምቁ አሉኝ እኔም ወደታዘዝሁበት ሥፍራ ሄጄ ሥርዓተ ጸሎት አደረስሁ ከዚያ በኋላ በጐርፍ ወደተቦረቦረው ሥፍራ ሄጄ ብመለከት ደረቅ አለት የነበረና ከዚያ ጠበል ይፈልቃል ተብሎ የማይጠበቀውን ወዝቶ አገኘሁት ፤ ከዚያ በኋላ በያዝሁት መስቀል ባርኬ በእጄም ዳስሼው ወደቤቴ ሄድሁኝ ።

ለታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፹፫ ዓ/ም አጥቢያ ሌሊት እንደልማዱ መጥቶ አነጋገረኝ ያንሥፍራጠዋት ሄደህ እየው ጠበሉ ፈልቆአልና ሕሙማኑም በዚያው እንዲጠመቁ አድርግ አለኝ እኔም እሺ አልሁኝ በበነጋታው እንደተነሣሁ በቀጥታ ወደሥፍራ ው ሄድሁኝ ጠበሉ ከደረቁ አለት መካከል አንድ ሜትር ያህል ፈንድቶ ዙሪያውን አጥለቅልቆት ተመለከትሁኝ በዚያን ጊዜ የምናገረውም አጣሁ ወደላይም ዘለልሁ ወደግራም ወደቀኝም ሮጥሁ ከደስታው ብዛት የተነሣም ለሰዎቹ እስክናገር ድረስ ቸኮልሁ ወደ ሰዎቹ ሄጄ እስክመለስ የሚሰወር እንጂ የሚቆይ አልመሰለኝም ቀደም ብሎ በቅዱስ ጊዮርጊስ ጠበል ሲታጠቡ ለነበሩት በሽተኞች ሔጄ ነገርኳቸው እየተሯሯጡ መጥተው ሲጠመቁ ልዩ ልዩ ደዌ የያዛቸው ሁሉ ወዲያውኑ የተፈወሱ ሔዱ አሁን ተፈውሰው የሔዱትም ለሌሎች በሽተኞች እየተናገሩ እነሆ ነገሩ እስከሩቅ ስለደረሰ ይህ ሁሉ በሽተኛ ሊመጣ ቻለ ብለዋል ። በዚሁ ወቅት በየቀኑ በዚህ ተአምረኛ ጠበል የሚጠመቁ ልዩ ደዌ የያዛቸው ሰዎች ብዛት ከአንድ መለስተኛ ገበያ ቢበልጥ እንጂ አያንስም ሕመምተኞቹም በልዩልዩ ደዌ ያሰቃያቸው ናቸው እጅና እግራቸውን በብረት ሙቅ ታስረው በቃሬዛ ተይዘው የመጡት ሁሉ ከጠበሉ ሲደርሱ በልዩ ልዩ ድምፅ እየጮሁ ለቀናል ሲሉና እያዳንዱ አጋንት



ነን ሌሎቹም ዛሮች ነን እኩሌቶቹም በልዩ ልዩ ደዌያት ተይዘናል እያሉ ሲለፈልፉና ሲድኑ ለመስማትና በዓይናችን ለማየት በቅተናል ።

ይህን ሁኔታ ለተመለከተው ባንድ በኩል የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ሲያስደስትና ሲያስደንቅ በሌላ በኩል ደግሞ አጋንንት በሰዎች ላይ እንዴት እንደሰለጠኑ ስናይ እጅግ በጣም ያሳዝናል ያሰቅቀናልም ።

ይህ ጠበል ከፈለቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ብዙ ሕሙማን ፈውሶአል ለምሳሌ ያህል ፤

| | | |
|---|---|---|
| ፩/ | ዕውራን | ፪፻ |
| ፪/ | ዛር የለከፋቸው | ፬፻ |
| ፫/ | የተለያዩ አጋንንት የያዙአቸው | ፫፻ |
| ፬/ | ሥራይ ያገኛቸው | ፪፻ |
| | ድ ም ር | ፩ሺ፩፻ |

አንድ ሺህ አንድ መቶ ሲሆኑ ቀለል ያለ በሽታ የያዛቸውም በርከት ያሉ ናቸው ።

በሽተኞቹም ከተለያዩ አውራጃዎችና ወረዳዎች እንዲሁም ከክፍላተ ሀገራት ከጎጃም ከትግራይ ከወሎ ከሸዋም ከሌሎችም ክፍላተ ሀገራት ሁሉ እንደሚመጡ ተረጋግጦአል ።

እንዲህ ዓይነቱ አስደናቂ ተአምራት ፣ ከተፈጸመላቸው መካከል ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን በግምት የ፳፩ ዓመት ወጣት የሆነ ከታወረ ሰባት ዓመቱ ነው የሚባል የዚህን ወጣት አባት ይህ ጠበል መፍለቁን ስለሰሙ ሊያስጠምቁ ሰኔ ፲፪ ቀን ፹፪ ዓ/ም ይዘውት ይመጣሉ እስፍራው እንደደረሱ ከጠበሉ ሳይጠመቅ አንድ ዓይኑ በራለት በበነጋታው ሰኔ ፲፫ ቀን ፹፪ ዓ/ም የአቡነ ዘርዓ ቡሩክ ዕለት ሁለተኛው ዓይኑ ተከፈተለት በዚህ ወቅት የነበረ የሕዝቡ ደስታና ውካታ እጅግ ድንቅ እንደሆነ የዓይን ምስክሮች ይናገራሉ ወጣቱ በአባቱ አማካይነት እየተመራ መጥቶ ከጠበሉ እንኳ ሳይጠመቅ በሥፍራው ብቻ በመድረሱ ባንድ ሌሊት ሁለት ዓይኖቹ በርተውለት ከአባቱ ጋር ወደ አገሩ ተመልሶአል ።

፪ኛ/ ቄስ ንጋቱ አስረስ የተባሉት ወጣት በሞጣ ጓትራን ኢየሱስ ደብር ሲያገለግሉ ሳለ አንድ አስማተኛ ይጣላቸዋል ። ከዚህ በኋላ አስማተኛው ከጋኔን ጋር ያቆራኛቸዋል ። ማለት በድግምት ያያይዛቸዋል ። ሁኔታው እንዴት እንደሆነ በጠበሉ ሲለፈልፉ አስማተኛ ው በጭልፊት ላይ ደግሞ ጭልፊቷን የሞተች አስመስሎ በሚቀድሱበት ቤ/መቅደስ ውስጥ ይጥላታል ፤ እርሳቸውም ሊቀድሱ ወደ ቤተመቅደሱ እንደገቡ ጭልፊቷን ሳያዩአት ይረግጧታል እግራቸው ለስልሶአቸው ጎንበስ ብለው ፣ ቢመለከቱ ጭልፊት ናት ይህች ደግሞ በየት ገብታ ነው እዚህ የሞተችው? ብለው አውጥተው ወደቅኔ መዓልቱ ይጥሏታል ።

ቄስ ንጋቱ ግብዓተ መንጦላዕት ደግመው ቅዳሴውንም ቀድሰው እንዳበቁና እትዉ በሰላም ተብሎ ሕዝቡን ካሰናበቱ በኋላ ጭልፊቷ ከወደቀችበት ሥፍራ ተነሥታ ትበራለች ጭልፊቷ ስትበር ቄስ ንጋቱም ልብሳቸውን ጥለው አብረው በረሩ ወደቤታቸውም አልተመለሱም ሁለት ዓመት አብደው ሲኖሩ ዘመዶቻቸው ይህ ጠበል እንደፈለቀ ሰምተው እጅና እግራቸውን አስረው ያመጡአቸዋል ። ሲጠመቁ ይህ ሁሉ ነገር ይዝረከረካል ። ይሁን እንጂ ጋኔኑ በእግዚአብሔር ኃይልና በቅዱሳን ጸሎት ከላያቸው ላይ ወጥቶ ሄዶአል ።

ቄስ ንጋቱ ጋኔኑ ከለቀቀላቸው በኋላ አንድ ሰባት ቀን ሌሎች በሽተኞችን እንዲያጠምቁ በራእይ ይነገራቸዋል ። በተነገራቸው መጠንም ሰባት ቀን ያጠምቃሉ በሰባተኛው ቀን ደግሞ ያንተ እግር በሚቆምበት



www.ethiopianorthodox.org

ሥፍራ ላይ የቅዱስ ሩፋኤል ጠበል ይፈልቃል ብሎ ይነግራቸዋል ።

ቄስ ንጋቱ አስረስ በነገሩ እየተደነቁ ወደ ጠበሉ ሥፍራ ይሄዳሉ በሥፍራው ለነበሩት ሰዎችም ሁኔታውን ይነግሩአቸዋል ። ሥፍራው የት እንደሆነ አላውቅም ያንተ እገር በሚቆምበት ሥፍራ የቅዱስ ሩፋኤል ጠበል ይፈልቃል ብሎኛል ብለው ሕዝቡ ለማጥመቅ ወደ ጠበሉ አካባቢ ሲደርሱ እግራቸው ባረፈበት ሥፍራ ላይ ባንድ ዕቃ እንደተቋጠረ ውኃ ፈንድቶ መላ ሰውነታቸውን አጥምቆአቸዋል ። በዚህ ጊዜ ቄታሲሙኽው ያውላችሁ የቅዱስ ሩፋኤል ጠበል ፈለቀላችሁ ብለው ለሕዝቡ አበሰሩ ፤ ሕዝቡም ለመጠመቅ ጋጋታውና ውካታው ተአምር ነበር ሲሉ አባ አድኅ አዋይተውናል በተጨማሪም በዚሁ ዓ/ም ከሌሊቱ በ፯ሰዓት አካባቢ ጀምር ከምሥራቅና ከምዕራብ የብርሃን ጎርፍ ወርዶ በጠበሉ ላይ ሌሊቱን ሙሉ ሲያበራ እንደሚያድር በአስተማማኝ ሁኔታ ገልፀውልናል ።

በዚህ ጠበል ዙሪያ የተለያዩ ጠበሎች ፈልቀዋል ይኸውም ፤

፩ኛ/ ዘርዓ ቡሩክ በመካከል

፪ኛ/ ኪዳነ ምሕረት በግራ

፫ኛ/ በዓታ በግራ

፬ኛ/ ቅ/ሩፋኤል በቀኝ

፭ኛ/ ቅ/ገብርኤል በቀኝ ይገኛሉ እነዚህ ሁሉ በአንድ ዓመት ውስጥ የፈለቁ ጠበሎች ናቸው ።

ከጠበሎቹ በላይ ፈጽሞ ደረቅ ዓለት እንጂ ርጥበት አይታይበትም እጅግ በጣም የሚያስደንቀውና የሚያስገርመውም ይህነው ጠበሉ አለቱን ቀዶ የወጣበት ሥፍራ ከአንድ ሜትር ያላነሰ ሲሆን የጠበሉን አጎራረፍም ዕፁብ ድንቅ ከማለት በቀር የሰው አእምር ሊደርስበት አይችልም ።



የጠበሉ አወራረድ የተጠማቂው ሥፍራ አመችነትም በጣም ግሩም የሆነ ነው ።

እንዲሁም በደብረ ማርቆስ ዙሪያ ከከተማው ፫ኪ/ሜትር ያህል ርቆ በሚገኘው ቀበሌ በጺድቁ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም የፈለቀ ጠበል ብዙ የተለያዩ ደዌ የያዛቸው ወገኖች በመፈወስ ላይ ይገኛል ።

ይህ ጠበል ከፈለቀ የ፲፱ ዓመት ዕድሜ ቢኖረውም በይበልጥ ባሁኑ ዘመን የሚያሳየው ገቢረ ተአምር እጅግ በጣም አስደናቂና አስገራሚ ነው ። በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዘው ለብዙ ዘመናት ሲሰቃዩ የኖሩት በሽተኞች ገና በሥፍራው ሲደርሱ በፍጥነት ይፈወሳሉ ።

በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ትእዛዝ በደብረ ማርቆስ አውራጃ ሊቀ ካህናት ስንሽው አግካይነት ሚያዝያ ፩ ቀን ፸፫ ዓ/ም የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጠኛ እስፍራው ድረስ ሄዶ ጎብኝቶታል ፤ በዚሁ ወቅት በሙቶ የሚቆጠሩ ተጠማቂዎች ተመልክቶአል ። የጋኔንና የዛር ልክፍት የያዛቸው ሰዎች እየለፈለፉ ሲወጡም አይቶአል ።

አንድ ግለሰብ በዛር ተለክፎ ለአምስት ዓመት ያህል ሲሰቃይ ከቆየ በኋላ በዚሁ ዕለት በጠበሉ ተጠምቆ እንደለፈለፈና እጅግ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ካንፈራገጠው በኋላ ጥሎት እንደሄደ ሰውየውም ትክክለኛ አእምሮ አግኝቶ ድና ወደ ቤቱ ለመመለስ እንደቻለ አረጋግጦአል ።

ከዚህም ሌላ አንዲት የሃያ አምስት ዓመት ወጣት ሴት ጋኔኑ ሁለት እግሮቿን አጣብቆ ሲያሰቃያት ከኖረ በኋላ በዚሁ ጠበል ተጠምቃ ሁለቱ እግሮቿ ተዘርግተው ለመቆም እንደበቃች ለማወቅ ተችሎአል ብዙ ሕሙማንም እየዳኑ ፈጣሪያቸውንም እያመሰገኑ ሲሄዱ ታይተዋል ።



የዚሁ ጠበል አጥማቂ አባ መሐሪ አወቀ ይባላሉ ፤ አባ የ፶ ዓመት አዛውንት ናቸው በድንግልናና በሕገ ምንኩስና ተወስነው በዚሁ አገልግሎት ጸንተው ከመኖራቸውም በላይ የሀብተ ጥምቀት ስጦታም ያላቸው ናቸው ። አጋንንት እርሳቸውን ሲያዩ ይብረከረካሉ ይጮኻሉ ከምን እንድረስ በየት ሥፍራ እንቀመጥ እያሉም ይዘላብዳሉ አባ ማጥመቅ ከጀመሩበት አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ስንት በሽተኞች እንደተፈወሱ ጠይቀናቸው ሲመልሱ ፩ሺ፩፪ ይደርሳሉ ብለዋል ። የርሳቸው ረዳትና አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ የሚያቀርቡላቸው የ፷፰ ዓ/ም አዛውንት የሆኑ አባ ገብረ ማርያም የኔነህ የሚባሉ መነኩሴ አብረዋቸው ይገኛሉ ። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ጠበሉ ከከተማው ሦስት ኪ/ሜትር ያህል ርቆ የሚገኝ ሲሆን በአካባቢውም መንደር የሌለበት የጽሞና ሥፍራ ነው ሥፍራው ለገዳማውያን አመቺ ነው ። ካሁን በፊት ቤ/ክርስቲያን አልነበረውም ።

አሁን ግን ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልገው መሆኑን ተረድተው የካቲት ፫ ቀን ፸፫ ዓ/ም በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም ቤ/ክርስቲያን ተክለውበታል ብፁዕነታቸው ስለወደፊት ያላቸው ዕቅድ እንዲገልፁልን ጠይቀናቸው ሲመልሱ ፣ ሥፍራው ለገዳማውያን መኖሪያ አመቺ ስለሆነ የወንዶችና የሴቶች ገዳም ለማድረግ እቅድ አለን ብለዋል ። መነኮሳቱ በምን ዓይነት ሁኔታ እንዲኖሩ ከዕቅዱ ጋር እንዲያብራሩልን ጠይቀናቸዋል ሲመልሱም የገበሬ ማኅበሩ ለገዳሙ የሚሆን ከልሎ የሰጣቸው መሬት በጣም ሰፊ ስለሆነ መሬቱ እየታረሰ በአዝርዕትና በአትክልት እየለማ ራሱን እንዲችል ነው ፤ ለዚህም መነኮሳቱ እንደየችሎታቸው መጠን ሠርተው ይጠቀሙበታል ይጠቅሙበታልም ። ይህም ማለት የማረስ የመቆፈር የአትክልት መትከልና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የማካሄድ ተግባር ያላቸው መነኮሳት በየቦታው ለማኖር ፍላጎት አለን ፤ ለጊዜው አሁን የሚያስቸግረን ነገር ቢኖር የበሬዎች መግዣ ገንዘብ ነው ። ከተቆናጠጠና ከደረጀ በኋላ ግን ርዳታም ጠይቀን ወፍጮና ሌላም በመነኮሳት ተግባረእድ እየተንቀሳቀሰ ልማት የሚሰጥ ሥራ ለማቋቋም ሰፊ ሀሳብ አሉን ብለዋል ።

አንባብያን በዚህ አጋጣሚ ልንጠቁመው የፈለግነው ነገር ቢኖር በልዩ ልዩ ደዌ ተይዛችሁ የምትሰቃዩ ወገኖቻችን ወይም የሚሰቃዩ ወገኖች ያሏችሁ ሁሉ ከላይ ወደተጠቀሱት ሥፍራዎች እየሄዳችሁ ፣ ወይም ወገኖቻችሁን እየወሰዳችሁ ያለ ዋጋ ደህንነትን አገኙ ፤ የእግዚአብሔር ቃል እናንተ ደካሞች ሁላችሁ ወደኔ ኑ እኔም ከድካማችሁና ከደዌያችሁ ሁሉ አሳርፋችሁኋለሁ እፈውሳችኋለሁ እያለ መንፈሳዊ ጥሪውን ያስተላልፋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# መዝሙረ ሆሣዕና–ትንሣኤ

የሆሣዕና ለት ጉዝጓዝ እንዲሆን
ከዘንባባ ቅጠል ከሰሌን ልጫን (ከሰል)
ከከሴውም ዘይቱን መድኃኒት ነው ካልሽ
ከሴም መድኃኒት ነው ጽዮን ልንገርሽ
(ሜም)

መድኃኒቱ ኢየሱስ መጥቶልሻል በገጽ
ሳለ የሚያድን ዕፅ ፤ ይቅርብሽ ፤የሚያምፅ

ዘንባባው ሊታደል ቤተ መቅደስ ገባ
ለበረከት ያህል ኸረ ስቲ ዘንባባ
(ማዘን መባባት)
ሰው አይገነዘብ የሰማውን ከልብ
ሳትረሳ ፈጣሪ-እባክህ ተገንዘብ
(ገንዘብ)
ከደብረ ዘይት መንገድ ቢታንያ ኋላ
ጉዝጓዝ ሆነ ምግቡ የተምሩ ዘለላ
ተምሩ አይደለም ድሮ የሚበላ
(ተምሮ ይበላል)

ያላዋቂ ማነው ውርንጫ ነው ያለ
ፈትታችሁ አምጡ እንጂ አህያው አድጎ
አለ
ድንጋይ በቃና ጠጅ፣ እድሜ ልኩን ሰክሮ
ሆሣዕና ደግሞ መድኃኒት ገስሮ
ይለፈልፍ ጀመር መንፈሱ ተዛውሮ
ከበሮ ቢንጋጋ ጸናጽል ቢሸካካ
ተጽዕኖ ካለ አይሆንም ፋሲካ
ካባትህ ቤት ገብተህ ሲነገድ ከምኵራብ
እርግባየህ አምላክ የካህንን ገንዘብ (ርግብ)
ገበያ እነጴጥሮስ አይተን አናውቅ ሲሉ
ካህናት በምኵራብ ገበያን አሉ (መገበያየት)
ወትሮዉንም ቢሆን የካህን ነጋዴ
አይቀርም እያደር ከመሆን ወምበዴ
ፈጽሞታልና ይሁዳው መደዴ
ክርስቶስ ዓለሙን አድኖት ሲያቀርብ
ምን ዋለለት ዓለም ባዳነው ገንዘብ

ከይቁም ገዛው
ገንዘብ ካልሠሩበት ባዳ ነው)
ጥቂት ነበር ጽዮን ላንቺ የሚበቃሽ
ባህያ ተጭኖ መድኃኒት መጣልሽ
ድንጋዩ ሊናገር አፉን ሲያባብስ ፤
እዩልኝ በሞቴ ቢኃያል ክርስቶስ
አይሁዶች ቅብዓ ዘይት ጽዮን ከሚያሹሽ
ባህያ ተቀምጦ ወልድ ቅብዕ ይሽሽ (መሸሽ)
ላህያ ጋላቢ ሜዳው መች ያልቅና
ፉት ሲሉት አይሁድ እንደ ይጋልቡና
(ቡናው ይጋል)
ጽዮን በቤትሽ ውስጥ ሻሽ ብቻ ነው ያለው
አምላክሽን ከግንድ በሻሽ ነው ያሠርሺው
(ስለሻሽ ስለፈለግሽ)
ከሳምንት እሳምንት ተወር ወር ድንጋይ
ለፍልፈህ ለፍልፈህ አይበቃህም ወይ
በሆሣዕና ድንጋይ ሲያመሰግን
(እየዘለለ ነበርና)
በየመነገዱ ዳር አሉ የታመሙ
ሐኪሞቹ እግሮችህ በመንገድ ካከሙ
(መካከም ማከም)
ወይን የመላበትን ያን ድንጋይ በቃና
ደግሞ ሞላበት ወይ ዛሬ ሆሣዕና
ኪሩቤሎች ላራት ያልቻሉትን ግርማ
ተሸክማው ሔደች አህያዩቱማ
ተረግረጊ ይታይ ጽዮን ተራራሽ
ቅብዕ ወልድ ዘላለሙን ካለ በራስሽ
(መራራስ ተራራ)
(በረጠ
ብሽ መራስ)

## አማርኛ መወድስ

በዘመነ ጊዜ ክርስቶስ ወደ ቀራንዮ
መኳንንተ ሕማም ወፃዕር ፈጥነው ከበ
ቡት ለአሥራ ሦስት ።



ፊት ወራሪ ጽፍአት በገጸ ወወሪቀ ምራቅ
ከፊት ።

ወተአሥሮ ድኅሪት ሲሆን በኋላ
ተቀሥፎ በጀርባ ወበጎን ኲናት ።

ወአክሊለ ሦክ የራስጌ ቤቱ
ወአፈንጉሥ ሐሞት፣ከራስ ተኰርዖ ጋር
ላዩን ገቡት ።

## ለ ዓ ለ ም

ለስምዖንሂ ጋሻ ዣግሬው ትእዛዝ ሰጠው
ድንገት ።

ፀዊረ መስቀል መትረየሱን ደግ ነው ብሎ
ወደ ጠላት ።

የሚተኵሰውም ክርስቶስ ቃታውን ቢይዝ
ድንገት ።

ቅንዋተ ሐፂን ወድቀው በእግሩ እጁንም
ጨብጠው ሰላም አሉት ።

ገና ወልድ ሳይሞት እንዳለ በስቃይ ።
ዕለቱን ፊትነሱት ጨረቃና ፀሐይ

የአዳምን በደል ታሪክ እየሰማሁ
እኔም በበኩሌ ሳይሞት እፈራለሁ

በየገበታው ላይ ከተዘረረው
እኔ እምጓጓለት ለተሰቀለው ።

ከሥጋው ሲሰጠን አምላክ ሲያድለን ።

ሰዉ ልብላ ይላል ያልታደለውን

የዛሬማ ሰዎች እንደመጽሐፉ ቃል ።

በድላችሁ ብሎ ያለውን ይዘዋል ።

መቃብር ብትገባም ወርደህ ከልዕልና ።
ሕዝብህ አቤት አቤት ይላል በትሕትና ።
አድራጊ ፈጣሪ ዳኛ አንተ ነህና ።

መቃብር ለሥጋው ሲያስብ ሲደንስ ።
ምንጊዜም ነፍስ አያውቅ እስኪያልፍ ድረስ
መቃብር ቢሰጠው ሥጋ ኢየሱስ
አልቀበል አለ ሥጋ አምላክ ላፈርስ ።

ሦስት ቀን ጾመኸ መቃብር ሕዝንት ።
እኔ አልቀምስም ብላ ወልድ የሞተዕለት ።

ያዋቂ ሞትና የፀሐይ ዕርበት

ለሁሉ ነውና የሚሆን ፀፀት ።

የማይታረም ነው ዘላለም መቃብር
ደግሞ አፉን ከፈተ በትንሣኤ ምድር ።

መቃብር ተከፍቶ አኩርፈው አይሁድ ።
ሳይበሉት ተነሣ የሥጋው ማዕድ ።

አምላክ ሳይቸግረው የሰው ሥጋ ለብሶ ፤
ባደባባይ ቆሟል በወንጌል ተከሶ ፤

አምላክ በአርአያው ሰውን ሲፈጥር ፤
እረግሞት ነበረ በረቂቅ ምሥጢር ።

ደግሞም በኋላ ወደደው ፤
አምላክ ሙት ኖሯል ለሥጋው ፤

ሰው አንድ ቀን ጋብዞ ፍርፋሪ እንጀራ ፤
ዘወትር ስሞታው ወቀሳው መከራ ፤

ሥጋውን በልቼ ብጠጣው ደሙን ፤
ሰሞታ አይወቅሰኝም ቸሩ አምላክ እኔን

አይሁድ ሸማኔዎች መሥሪያ አጣን ይላሉ ፤
ጥበብ መሥሪያቸውን ዓርብ እየሰቀሉ ፤

ለወልድ ያላዘነ ምን ፍጡር ይገኛል
ጨረቃ ዘመዱ ፊቱን ሲነጭ አድሯል ።
ፀሐይም ወገኑ ማቁን ለብሶ ውሏል ።

ፀሐይም ቆሟለ አዞሮ ፊቱን
ጨረቃም ቆሟለ መልሶ ፊቱን
ጌታ ወልድ ሲመገብ ስቅለት ማዕዱን

በሰማይ በምድርም በዓለም ክበብ



www.ethiopianorthodox.org

ከሱ በላይ የለሚያውቅ ጥበብ

ስለአንድ ልጁ ሞት እያወቀው አብ
ዐርብ ዕለት አስቦ ገደፈ ኮከብ ፤

መቃብር ከፈተ ኮከብም ገደፈ
አንድ ልጁ እንደሆን ከዓርብ አላለፈ ።

ኮከብ ሰማይ ሰማይ ሲዘል የነበረ
ዛሬስ ወደመሬት አዝኖ አቀረቀረ ።

የሰገሉ ኮከብ ከሰው ጋር አንድነት

የጠየቀው ወልድን የተወለደለት

ከምድር ወርዶ ተኛ ደግሞ የሞተለት

መስቀል ፈረሱን ወልድ የገራለት
መሳቢያው ፍቅር እርካቡ ቀኖት
ግላሱ የተምር ምቹ የህለት
ቀዳማዩ ጦር ዳራው ግርፋት
አጥብቆት ኖሮ የአይሁድ ቅንዓት
ኮከብ አሸከሩን ጣለው ከመሬት

የገሊላው ወልድ የዓለም ጌታ
መስቀል ፈረሱን የጫነ ለታ
ቅርሳይሰኝ ሳያመነታ
ከሲኦል ወርዶ የማታ ማታ
ሞትን ድል ነስቶ አርጎ ይቅርታ
የታሠሩትን በሙሉ ፈታ ።



# ማ ዕ ዶ ት

ይህ መጽሔት በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ በመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት በስብከትና ማስታወቂያ መምሪያ እየታተመ ይወጣል ።

## የመጽሔቱ ዕድገት ጠባቂዎች

፩ኛ/ አቶ መርስኤ ኅዘን አበበ የጠ/ቤተ ክህነት ተ/ ዋና ሥ/አስኪያጅ
፪ኛ/ መምህር ብርሃኑ ካሣ የስብከትና ማ/መምሪያ ኃላፊ
፫ኛ/ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/ ዐማኑኤል የትንሣኤ /ዘጉ/ማ/ቤት ሥራ አስኪያጅ
፬ኛ/ ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳን ካሣ የትም/ማሠ/መምሪያ ኃላፊ
፭ኛ/ አቶ ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም የስ/ትና ማስታወቂያ መምሪያ ዋና ጸሐፊ

## አ ዘ ጋ ጅ

የስብከትና ማስታወቂያ መምሪያ
ፖስታ ሣጥን ቁጥር 1283
ስልክ ቁጥር 11 07 54 አዲስ አበባ ፤

## ማ ው ጫ ፤


| ተራ ቁጥር | አ ር እ ስ ት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፫—፭ |
| ፪ | የፓትርያርኩ መልእክት | ፮—፯ |
| ፫ | የቅዱስነታቸው ጉብኝት | ፰—፲፱ |
| ፬ | ያችን ሰዓት | ፳—፳፫ |
| ፭ | ሰሙነ ሕማማት | ፳፬—፳፯ |
| ፮ | በመስቀሉ ደም | ፳፰—፴ |
| ፯ | ኢሃሎ ዝየሰ ተንሥአ | ፴፩—፴፪ |
| ፰ | ማዕዶት | ፴፫—፴፰ |
| ፱ | በዓለ ሃምሳ | ፴፱—፵ |
| ፲ | ተአምራታዊው ጠበል በጎጃም | ፵፩—፵፭ |
| ፲፩ | ከሆሣዕና -- ትንሣኤ አማርኛ ግጥም | ፵፮ |


www.ethiopianorthodox.org